# የሥነ - ጥበባት ትምህርት የመምህሩ መምሪያ

# 1ኛ ክፍል


**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች**

ደንደኣ ቦጋለ

ደሜ ቶሊና

ታደሰ ድንቁ

**አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

ሉባባ ጀማል

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሰን

**ተርጓሚ**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

**ኤዲተር**

ደቀቦ ጉዬ

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገላጭ ስዕል**

ቡዛዮ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝቶ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

ማውጫ


**ምእራፍ 1: የስነ ጥበብ ግንዛቤ** .......... 1

1. የስዕሎች መልዕክት .......... 2

1.2 መዝሙሮችን ማየት፣ መስማትና መዘመር .......... 4

1.3 ምስለ ድምፅ መመልከትና መስማት .......... 10

**ምእራፍ ሁለት የፈጠራ ችሎታ** .......... 16

2.1. የሰማይና የምድር ፍጥረት .......... 16

2.2. የቤተሰብ የስራ ድርሻን ማስመሰል .......... 17

2.3. መስመሮችን በማስመር ማቅለም .......... 20

2.4. የቤተ-ሰብ መዝሙር .......... 27

**ምእራፍ ሶስት: የታሪክና የባህል ተጨባጭ ሁኔታ/** .......... 35

3.1 የህብረተሰቡና የአካባቢ ሙያዎች .......... 35

3.2 የባህል መዝሙር .......... 37

3.3 ተረት ተረት .......... 41

**ምእራፍ አራት : የስነ ጥበባት ማራኪነት** .......... 49

4. አስደናቂ የባህል ክንውኖች .......... 49

4.1. የቤተሰብ መዝሙርና ውዝዋዜ .......... 49

4.2. የቤተሰብን የስራ ድርሻ በድራማ መልክ መግለጽ፡፡ .......... 50

4.3 የቤተሰብ ስእል ........................................................................................ 55

**ምእራፍ አምስት: የስነ -ጥበባት ግንኙነት** .................................................... 57

5.1. መዝሙር በቡድን በመዘመር የራስን ተፈጥሯዊ ድምፅ ማሳደግ ....................................... 57

5.2. የታሪካዊ ቦታዎች ግንኙነትና ትግበራ........................................................................ 61

## አጠቃለይ መግቢያ

በመማር እና ማስተማር ሂደት ውስጥ፤የእያንዳንዱ ተማሪ ተሳትፎ እንዳይወሰን፤መምህር ሁሉንም ቡድን በመቆጣጠር ፣መርዳት፣መምራት እና ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ስለዚህ መምህር/ርት በትምህርት ዉስጥ ሁሉም ተማሪዎች ሃሳብ በመስጠት፣መወያየት እና በመከራከር ዕዉቀት፣ግንዛቤ እና ያላቸዉን ልምድ በመለዋወጥ የሚፈለገዉ የትምህርት ዉጤት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አለብህ/ሽ፡፡ መምህር/ርት የሥነ ጥበብ ትምህርት ሲታስተምር/ሪ መግቢያ፣አቀራረብ፣ማጠቃለያ እና ዓላማ ከማቀድህ/ሽ በፊት መፈፀም ያለባቸዉን ድርጊቶችን በደንብ ማዘጋጀት እና መፈፀም አለብህ/ሽ፡፡

### ሀ.በመግቢያ የሚፈፀሙ ድርጊቶች

ተማሪዎች ያለፈዉን የትምህርት ይዘት፤ በደምብ መማራቸዉን ለማረጋገጥ መምህር/ርት የተለያዩ ከትምህርቱ ጋር የተያያዛቱን ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ከዕለቱ ትምህርት ጋር ማያያዝ አለብህ/ሽ፡፡ በተለይ ለተጠየቁት ጥያቄዎች በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች እድል በመስጠት፤ መልስ ላላገኙት ጥያቄዎች ደግሞ ጎበዝ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ ማድረግ እና ሁሉም ተማሪዎች ለትምህርት እንዲዘጋጁ፣ክፍል ዉስጥ እንዲሳተፉ፣ እንዲመወዳደሩ እን በትምህርቱ ጎበዝ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ከዕለቱ ትምህርት ጋር ተያይዘዉ፤ ተማሪዎች ቀድሞ ያላቸዉ ዕዉቀት (prerequiste knowledge) ማወቅ እና አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤ተማሪዎች ሃሳብ እንዲሰጡበት በማድረግ እንዲሁም የዕለቱ ትምህርት ጠቀሜታ/ፋይዳ፣አስፈላጊነት እና ዓላማ ጋር በማስተዋወቅ ተማሪዎች እና እንዲዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

### ለ.በአቀራረብ የሚፈፀሙ ድርጊቶች

በመማር እና ማስተማር ሂደት ትምህርቱ ሲቀርብ

- በይዘት እና ዓላማ ላይ በመመሥረት፤ በአነስተኛ ቁጥር ቡድን በማደራጀት እና በርዕሱ ላይ እንዲወያዩ መምራት፡፡
- አንኳር የሆኔ የመወያያ ነጥብን ከትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማ ጋር እንዲሄድ ለቡድኑ በተዘጋጀ ጥያቄዎች መሰረት በሳሌዳ ላይ መጻፍ፡፡
- መምህር/ርት እያንዳንዱን ቡድን መማራቸዉን መከታተል፣መምራት፣ማገዝ እና መቆጣጠር አለብህ/ሽ፡፡

**በቡድን እና ክፍል ዉስጥ ያላቸዉን የእያንዳንዱ ተማሪዎች ተሳትፎ መከታተል እና ማበረታታት፡፡**

- በአነስተኛ ቡድን የተወያዩበትን ወይም የሰሩትን ነገር፣ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተራ በተራ በተለያየ የትምህርት ጊዜ እንዲያብራሩ በማድረግ ተሳትፏቸዉን እንዲጨምሩ ማድረግ ነዉ፡፡
- ተማሪዎች ከተወያዩ/ ከሰሩ በኋላ ያቀረቡት አንኳር ነጥብ በሳሌዳ ላይ መፃፍ፡፡
- የትምህርቱና ይዘት ከአከባቢያቸዉ ጋር በማያያዝ እና በመርጃ መሣርያ በመጠቀም የእለቱን ትምህርት መተንተንእና መመዘን፡፡

***ሐ.በማጠቃልያ የሚከናዉኑ ድርጊቶች***

- የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ስኬትን ለማረጋገጥ የክፍል ስራ፣የቤት ስራ፣ፕሮጀክት እና የመሳሰሉትን በቡድን፣በጥንድ እና በግል እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- የክፍል ስራ እና የቤት ስራ ለሰሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጉትን ግብረ-መልስ መስጠት፡፡
- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ፕሮጀክት እና የመሳሰሉት ተሰጥቷአቸዉ መመለስ ላልቻሉት ተማሪዎች የተለየ እገዛ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማርዎችህ/ሽ የሚቀጥለዉን ትምህርት አንብቦ አንድመጡ ምራቸዉ፡፡

***መ. ትምህርቱን ዕቅድ ከማቀድ በፊት***

በመማር እና ማስተማር ሂደት ዉስጥ የስነ ጥበብ መምህራን የትምህርቱን ይዘት ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንዲሁም ሙያቸዉን ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻል አለባቸዉ፡፡ ማንኛዉም የተማረ ሰዉ፣የማያነብ/የማይለማመድ ከሆነ የሚያስተምረዉን ትምህርት መርሳቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ይህን ክፍል የሚያስተምሩ የስነ ጥበባት መምህራን የሚከተለዉን የስራ ድርሻ እና ሃላፊነት ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለባቸዉ፡፡

- ለዕለቱ የታቀደ የትምህርት ይዘት ወይም ለማስተማር የተዘጋጀዉን በደንብ ማንበብ እና መገንዘብ፡፡
- ከተማሪዎች መፅሐፍ ለማስተማር የታቀዱትን ትምህርት ጋር የተያያዘዉን እጭር ማስታወሻ መፃፍ፡፡

- ለዕለቱ ትምህርት በተማሪዎች መፅሐፍ የተገለፁት በቂ ካልሆነ፤ ከ5-8 ክፍል ለሚያስተምሩ የስነ ጥበብ መምህራን የተዘጋጀ ማኑዋል ወይም ከተለያዩ የዋቢ መፅሐፎችን ማቀናጀት፡፡
- በተማሪዎች መፅሐፍ ዉስጥ የሚገኙ ሙከራዎች፣ድርጊቶች፣መልመጃዎች እና የክለሳ ጥያቄዎችን ቀድመዉ መስራት፣መሞከር እና መለማመድ አስፈላጊ ነዉ፡፡

# ምእራፍ 1: የስነ ጥበብ ግንዛቤ

## ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ........25

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የአካባቢያቸውን ድምፅ ሥዕልና የቤተሰቦቻቸውን አበላትና የልጆች ጨዋታዎችን በመጨወት ይለያሉ፡፡
- የመንገድ ደህንነትና የትምህርት ቤት ሥዕል በማየት ያደንቃሉ፡፡
- የተለያዩ ቀላል የድርጊት መዝሙሮችን በማስመሰል ይዘምራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚገኙትን የስነ-ጥበባት ስራዎችን ይገልፃሉ፡፡
- የስነ ጥበባት ሙያ ስራዎችን ያደንቃሉ፡፡

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ የስነ-ጥበብ ግንዛቤ በሚለው ርዕስ ስር የቤተሰብ ስእል ምልከታ፣የልጆች ጨዋታ፣ ልጆችን መምከር፣ የመንገድ ደህንነት ስዕል፣ መዝሙሮችን ማዳመጥ፣ የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት መዝሙር እና ምስለ-ድምፅን መመልከትና ማዳመጥን በውስጡ ያቀፈ ነው፡፡ ይህ የስነ-ጥበባት ግንዛቤ ልጆች አካበባቢያቸውን እንዲገነዘቡ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ፡ልጆች እንዴት የመኪና መንገድ/ወንዝ ማቋረጥ እንዳለባቸው ከቀረበው ስዕል ይገነዘባሉ፡፡ በተጨማሪም ት/ቤትን ለተማሪዎች ምቹ በማድረግ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲወዱ ያደርጋል ፡፡ይህም በጨዋታ፣ በመዝሙርና በትያትር መልክ በማስተማር በቀላሉ አካባቢያቸውን እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

# 1. የስዕሎች መልዕክት

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 8 ነው፡፡

ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸው የመማር ብቃት፡

በዚህ ርዕስ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የቤተሰባቸውን አበላትይናገራሉ፡፡
- የልጆችን ጨዋታ በመጫወት ያሳያሉ፡፡
- በትምህርት ቤት ውስጥ ምን እንደሚገኝ ይለያሉ፡፡
- መንገድን እንዴት እንደሚያቋርጡ /እንደሚሻገሩ ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡

## መግቢያ

ምልከታ ማለት ማስተማር የተፈለገውን ነገር በአካል በቅርበት በመገኘት እንዲገነዘቡ ያስችላል፡፡ በምልከታ ጊዜ በመማሪያ ክፍል፣ በት/ቤት ግቢና በቤታቸው ውስጥ የማይገኙ ነገሮችን በቅርበት/በአካል በመገኘት የሚማሩበት ዘዴ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ጋር እንዲተዋወቁ ይረዳል፡፡ ለምሰሌ፡ ተማሪዎች የቤተሰቦቻቸውን አበላት፣ እንዴት እንደሚጫወቱ፣ እንዴት ወንዝና የመኪና መንገድ እንደሚሻገሩና የመሳሰሉትን እንዲለዩ ያደርጋል፡፡

## የመጀመሪያ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የቤተሰብ አበላት፣ የልጆች ጨዋታ፣ የልጆች ምክር፣ ት/ቤት ፎቶና የመንገድ ደህንነት እንቅስቃሴን የሚያሳዩ ሥዕሎችን፡፡ የመጀመሪያውን ዝግጅትዎችን ከጨረሱ በኋላ የስነ ጥበባትን ክፍሎች ስነ-ትዕይንት፣ ስነ-ትያትር፣ ሙዚቃና ውዝዋዜ መሆናቸውን ለተማሪዎች በመንገርና በመዘርዘር በመንገር የዚህን ትምህርት ምዕራፍ ትምህርት ይጀምሩ፡፡

## 1. የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ምልከታ
- የግልና የቡድን ጨዋታ
- ማብራሪያ
- ጥያቄና መልስ

## 2. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የተለያዩ ስዕሎች
- መለማመጃ ክፍል
- የምስለ ድምፅ (ቪድዮ) መጨዋቻ

## 3. ተከታታይ ምዘና

- የግልና የቡድን ፅብረቃ/ገለጻ
- የክፍል ውስጥ ልምምድ
- የቤት ስራ
- ቃለ መጠይቅ
- የተማሪዎችን መማሪያ ደብተር ማየት

## 4. የመምህር ድርሻ

- አካባቢያቸውን በደንብ እንዲያስተውሉ ይንገርዋቸው፡፡
- የግቢያቸውና የትምህርት ቤታቸውንና መስብህነት እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡
- በተፈጥሮ በግቢያቸው አካባቢ የሚገኙ ነገሮችን በእንክብካቤ እነዲይዙና እንድጠቀሙበት ያድርጉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚገኙትን ነገሮችን እንዲጠይቁ፣ እንዲገልፁ እና እንድነጋገሩ በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 1.1. የተለያዩ ምስሎች መልእክት

በዚህ ትምህርት ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች የተለያዩ ምስሎችን በመመልከት መልዕክታቸውን እንዲለዩ ማድረግ

**የመምህር ድርሻ**

- ተማሪዎቹ ተመልክተው ከተመለሱ በኋላ በተመለከቱት ስዕሎች ላይ የራሳቸውን ሃሳብ እንድሰጡ ያድርጉ፡፡
- በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የተሰጠውን ስዕል እንዲመለከቱ በማድረግ መልእክቱን እንዲለዩ አግዙ፡፡

መምህር ልጆች ከዚህ ምስል ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡ ለምሳሌ- ቤተሰብ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ሆነው ቡና እያፈሉ ሳሉ የሚፈጽሙትን ስራዎች፣ በአንድ ቤተሰብ ግቢ ውስጥ ያሉ ነገሮች፣ ትምህርት ቤት ሲሄዱ እንዴት የመኪና መንገድ እንደሚያቋርጡ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ያለውን መንገድ ደህንነት የሚያሳየውን ምስል ማየትና የመሳሰሉትን ማከናወን ናቸው፡፡

ልጆች የሚያውቁትን የቤተሰብ ምስል፣ የልጆች ጨዋታ፣ ት/ቤት፣ የመንገድ ደህንነትና የመሳሰሉትን ምስሎች በመመልከት ወይም ቤተሰብ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ እንዲጫወቱ ማድረግና ከምስሎቹ ምን ምን እንደተማሩ አንዱ ለሌላው እንዲነግር በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 1.2 መዝሙሮችን ማየት፣ መስማትና መዘመር

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ……..9**

**መግቢያ**

ልጆች ትምህርታቸውን ቀለል ባለ ሁኔታ መማር አለባቸው፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም በጨዋታ መልክ በመዘመር/በመዝፈን ቢማሩ በአካባቢያቸው አዲስ የሆኑባቸውን ነገሮች በቀላሉ እንዲረዱና መቸም ቢሆን እንዳይረሱ ያደርጋል፡፡

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸው ብቃቶች**

ከዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡

- የተለያዩ መዝሙሮችን የመዘመር ችሎታቸውን ያሳያሉ፡፡
- ከመዝሙር ጋር በማያያዝ በዙሪያቸው ያሉትን ነገሮች ይገልፃሉ፡፡

## የምእራፉ ዋና ዋና ነጥቦች

- ☞ የማንበብ መዝሙር
- ☞ የፀሐይ መዝሙር
- ☞ የትምህርትቤት መዝሙር
- ☞ የአማርኛ ፊደላት መዝሙር
- ☞ የቤተሰብ አበላት መዝሙር

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ከበሮ
- ክራር
- መሰንቆ
- ኪቦርድ
- ዋሽንት
- በአካባቢያቸው የሚታወቁ ለህፃናት ተጨማሪ መዝሙሮችን ማዘጋጀት

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

መምህር መዝሙሩን ለማስተማር ከተማሪዎች ጋር በመሆን ተማሪዎች እንድለማመዱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎችዎ የመዝሙሩን ግጥም በሚገባ እስኪይዙ መስመር በመስመር ያለማምዷቸው፡፡ ፈጣንና ቀስተኛ ተማሪዎችን በመለየት ፈጣን ለሆኑ

ተማሪዎች ተጨማሪ ስራ በመስጠት ደከም የሚሉትን ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት ያግዟቸው፡፡ በየቀኑ የሚያሳዩትን ለውጥ ይከታተሉ፡፡

# ተከታታይ ምዘና

## የመምህር ድርሻ

መምህር በተማሪ መፅሐፍ ***ማንበብ እወዳለሁ*** የሚለውን መዝሙር ለማስተማር

- የኢትዮጵያ ልጆች ጨዋታ ከሚለው ቪድዮ በመውሰድ ወይም ዜማውን በራስዎ በማዘጋጀት አስቀድመው እርሶ በሚገባ ይለማመዱ፡፡
- ተማሪዎች የመዝሙሩን ግጥም መስመር በመስመር በመቀጠል በኋላ ተማሪዎችዎን ያለማምዱ፡፡ በሚገባ ካለማመዷቸው በኋላ በራሳቸው እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

የልጆች ጨዋታ መዝሙር 1

ማንበብ እወዳለሁ

**ማንበብ እወዳለሁ**

**ሁልግዜ አነባለሁ**

**ባነበብኩኝ ቁጥር**

**ይገባኛል ሚስጥር፡፡**

**ሚስጥር ሚስጥር/×2**

**የእውቀትን ሚስጥር**

**እኔ ልንገራችሁ**

**ከየ መፅሀፍ ታገኙታላችሁ፡፡**

**ሚስጥር ሚስጥር/×2**

ከዚህ በላይ ያለውን መዝሙር በዜማ በተቻለ መጠን ተማሪዎች ዜማውን በደንብ እንዲያዙና እንዲዘምሩ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀሙ፡፡

ለምሳሌ በተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ ባለው የፒያኖ ኪቦርድ ላይ በመጫን

የልጆች ጨዋታ መዝሙር 2

ፀሐይ ፈነጠቀች

መምህር ፀሐይ ፈነጠቀች የሚለውን የልጆች መዝሙር አስቀድመው መዝሙሩን የኢትዮጵያ ልጆች ጨዋታ ከሚለው ቪድዮ በመውሰድ ወይም ዜማውን በራስዎ በማዘጋጀት አስቀድመው እርሶ በሚገባ ይለማመዱ፡፡ከዚያም የመዝሙሩን ግጥም ከዜማው ጋር መስመር በመስመር ያለማምዷቸው ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎቹ በብድናቸውና በአንድ ላይ እንዲዘምሩት ያድርጉ፡፡

## የልጆች ጨዋታ መዝሙር 3

## ትምህርት ቤቴ

መምህር ትምህርት ቤቴ የሚለውን መዝሙር በዜማ መስመር በመስመር በደንብ ካለማማዷቸው በኋላ በቡድንና በአንድነት እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡ ልጆቹ በሚለማመዱበት ወቅት ድምፃቸው በጣም ወጥቶ በሌሎች ክፍሎች የሚማሩ ተማሪዎችን እንዳይረብሹ በመካከለኛ ድምፅ እንዲለማመዱ ያደርጉ፡፡ መዝሙሩ እንደሚከተለው ቀርቦሎታል፡፡ በባዶ ቦታው ላይ የትምህርት ቤታቸውን ስም በመሙላት ይዘምሩ፡፡

…ትምህርት ቤቴ<br>
ያደኩብሽ<br>
የተማርኩብሽ<br>
ኑሪ ለዘላለም<br>
እንደኮራሁብሽ 2x

…ትምህርት ቤቴ

የእውቀት ገበታዬ
አንቺ ስለሆንሽ
የምታሳድጊኝ
በእውቀት ኮትኩተሽ
ዛሬም ነገም ሁሌም እኔ ወድሻለሁ
እድገትና ልማት እመኝልሻለሁ፡፡

አስተማሪዎቼ ይግባችሁ ምስጋና
እውቀት የምቀስመው ከናንተ ነውና
ዛሬም ደጋግሜ አመሰግናለሁ
ሀ ለ መ ሰ ብዬ መቁጠርን ችያለሁ×2

የዚህን መዝሙር ዜማ በፒያኖ ኪቦርድ ላይ ወይም በተንቀሳቃሽ ስልክ ሶፍትዌር በመጠቀም ተማሪዎችን ያለመምዱ፡፡

የልጆች ጨዋታ መዝሙር 4

የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት

መምህር አስቀድመው የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት የሚለውን መዝሙር ከቻሉ በራስዎትወይም ዜማ የመድረስ ችሎታ ያላቸው መምህራን ወይም ሌሎች ሰዎች በመጋበዝ ቀለል ያለ ተማሪዎች በቀላሉ ሊይዙት የሚችሉት ዜማ ይስሩለትና አስቀድመው እርሶ በደንብ ተለማመዱ ፡፡


- ይህንን የትምህርት ክፍል በሚያስተምሩበት ክፍለ ጊዜ አስቀድመው ተማሪዎችዎ ካሁን በፊት ስለ አማርኛ ቋንቋ ፊደላት የተዘመሩ መዝሙሮች ሰምተው ያውቁ እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡ የሚያቁትን የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት መዝሙር እየተነሱ እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ለክፍለ ግዜው የተዘጋጀበትን መዝሙር ያለማምዷቸውና በቡድንና በአንድነት እንዲዘምሩት ያድርጉ፡፡ በልምምድ ወቅት ደከም የሚሉ ተማሪዎች ካሉ በማገዝ ከሎሎቹ ተማሪዎች ጋር አብረው እንዲለማማዱ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም ለክፍሉ ተማሪዎች ሁሉ አድናቆትዎን ገልፀው የእለቱን ትምህርት ያጠናቁ ፡፡

## የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት መዝሙር

ሀ ለ መ ብዬ መቁጠር ጀመርኩ
ሰ ረ ሸ በማለት አስከተልኩ
ቀ በ ተ የፊደል አካላት
ቸ ነ ኘ የመሀል ፊደላት
አ ከ ወ ብዬ ቀጥላለሁ
ዘ ዠ ገ ን ደሞ አስከትላለሁ
ደ ጀ የ ለማለት አልደክምም
ጠ ጨ ፀ ን ሳልቆጥር አላልፍም
ጰ ፈ ፐ ብዬ አሳርጋለሁ
ፊደላትን ሁሉ እዲህ እማራለሁ፡፡/ 3

### የልጆች ጨዋታ መዝሙር 5

### የሙዝ መዝሙር




መምህር ከዚህ በታች ያለውን የቁጥር መዝሙር ግጥሙን መስመር በመስመር ለተማሪዎች ይንገሯቸው እነሱም በቃል እየተቀባበሉ በቡድንና በግል በመዝሙሩ ውስጥ ያሉትን ቃላት ካወቁ በኋላ ዜማው አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት ስላለው በዚያው አይነት መዘመር እንዲችሉ እርሶ ቀድመው በመዘመር ያለማምዷቸውና በግልና በቡድን እንዲለማመዱና አንዱ ለሌላው እንዲያሰማ በማድረግ ያከናውኑ፡፡

መዝሙሩ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ይገኛል፡፡

## 1.3 ምስለ ድምፅ መመልከትና መስማት

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት 8 ነው፡፡

| |
|---|
| ቢያንስ ተማሪዎች መጎናፀፍ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች<br>ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>- ምስለ ድምፅን በማየትና በመስማት ዘና ብለው የመረዳት አቅማቸውን ያሳድጋሉ፡፡ |

የዚህ ትምህርት ይዘት አበይት ነጥቦች

- በደስታ የሚዘፍኑ የልጆች ምስለ ድምፅ/ ቪድዮ/
- የቤተሰብ መዝሙር ምሰለ ድምፅ/ቪድዮ/
- የቀዩ ጫማ ምስለ ድምፅ/ቪድዮ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ቪድዮ የሚመለከቱበት ክፍል
- የቪድዮ ሲዲ ወይም ፍላሽ
- የቪድዮ ማጫወቻ

የማስተማሪያ ዘዴ

መምህር አስቀድመው የኢትዮጵያ ልጆች ጨዋታ ከሚለው ቪድዩ ደስተኛ የሆነ በሚል ርእስ የተሰራውን ቪድዮ በስልኮ ወይም ለእርሶ በሚቀሎት መንገድ በመውሰድ ያዘጋጁ፡፡ በቪድዮው ህፃናት እየዘመሩ ደስታቸውን ሲገልፁ የሚዘምሩትን መዝሙር ከዜማው ጋር አስቀድመው እርሶ በሚገባ ይለማመዱ፡፡

ይህንን የትምህርት ክፍል በሚያስተምሩበት ወቅት በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ የተመለከቱትን የምስለ ድምፅ/የቪድዮ ምስል ተማሪዎች እንዲመለከቱና ስለ ምስሉ የተረዱትን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል በስልኮ ወይም በሌላ ዘዴ የቀረፁትን ቪድዮ ለተማሪዎችዎ አሳይዋቸው፡፡ ካዩት ምስለ ድምፅ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡ ከዚያም የመዝሙሩን ግጥም ከዜማው ጋር መስመር በመስመር ያለማምዷቸው ተማሪዎቹም በቪድዮ እንደሚመለከቷቸው ተማሪዎች በተለያየ መልክ መዝሙሩን እየዘመሩ ደስታቸውን እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ ምሰለ ድምፁን ማግኘት የማይችሉ ከሆነ መዝሙሩን በራስዎ ወይም ሌላ ሰው በመጋበዝ ዜማ ሰርተው ተማሪዎቹ እየዘመሩ ደስታቸውን እንዲገልፁ ያበረታቷቸው፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች ቪድዮ በመመልከትና በመስማት ውስጥ

- መልእክቱን በጥልቀት መረዳት
- ለሚተላለፈው መልእክትና መመሪያ ግብረ መልስ መስጠት
- ሀሳቦችንና አመለካከቶችን መከፋፈል ችሎታዎችን ለመዳበር የሚረዳቸው ስለሆነ በተቻለ መጠን የሚያዩት ነገር ቢዘጋጅላቸው በጣም ጥሩ ነው፡፡

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ

ቸብ ችብ

ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ

ችብ ቸብ

ደስተኛ የሆነ ይደንስ

ዳንስ ዳንስ

ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ ይደንስ

ዳንስ ዳንስ

ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ

ሀ ሀ ሀ

ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ

ሀ ሀ ሀ

ደስተኛ የሆነ ወደላይ ይዝለል

ዘለል ዘለል

ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ ወደ ላይ ይዝለል

ዘለል ዘለል

ደስተኛ የሆነ ይዘምር

ሻላላ

ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ  ይዘምር

ሻላላ

ድስተኛ የሆነ ሁሉን ይበል

ቸብ ቸብ ዳንስ ዳንስ ሻላላ

ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ

ደስተኛ የሆነ  ሁሉን ይበል

ቸብ ጭብ ዳንስ ዳንስ ሻላላ



## ስለ ቤተሰብ አበላት መዝሙር..............

የቀዩ ጫማ ምስለ ድምፅ (ቪ.ድዮ)

መምህር በተማሪ መፅሐፍ ያለውን ቀይ ጫማ ስእል እንዲመለከቱ ካደረጉ በኋላ ስለምን እንደሚመለከቱ እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል የቀዩን ጫማ ቪድዮ " youtub" ላይ መውረድ ይችላሉ፡፡ ከዚያም ለተማሪዎችዎ እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ቪድዮውን ከተመለከቱ በኋላ ምን እንደተረዱ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

ታሪኩ እንዲህ ነው፡፡

*ደራርቱ በልጅነቷ ከእናትዋ ጋር ትኖር ነበር፡፡ እናትዋ በጣም ትታመም ነበር፡፡ ሀብትም አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ እናቷ ከእንጨት ጫማ ትሰራላት ነበር ፡፡ ካራን ግን ከእንጨት የሚሰራውን ጫማ አትወድም ነበር፡፡ ደራርቱ አንድ ቀን በሳጥን ውስጥ የተቀመጠ ቀይ ጫማ አገኘች፡፡ ጫማውን ከሳጥን ውስጥ አውጥታ ለእናቷ ስታሳያት እናተዋም በሰው ንብረት መጠቀም እንደሌለባት ከነገረቻት በኋላ ጫማውን እንዳትጠቀም ከለከለቻት፡፡ እናትዋም ህመምዋ በረታባትና ከሳምንት በኋላ ሞተች፡፡ በእናትዋም መቃብር ላይ ቀዩን ጫማ አድርጋ ተገኘች፡፡ በለቅሶው ላይ የተገኙ አንድ አሮጊት በእናትዋ ለቅሶ ላይ ቀይ ጫማ ማድረግ እንዳልነበረባት ነግራት አውልቃ እንድትጠል አደረገቻት፡፡ ልጅቱን ሊያትዋ ልታሳድጋት ወስዳት ገባች፡፡*

*ደራርቱ ሊያቷ ጋ ስታድግ ፀባይዋ ሁሉ እየተቀየረ መቷል፡፡ አስቸጋሪ ፀባይ ያላት ልጅ ሆነች፡፡ ሊያትዋ ተንከባክባ ብታሳድጋትም እሷ ግን ምክሯን አትሰማም፡፡ ሊያትዋ ደክማ የምታዘጋጅላትን ምግብ አትወድም፡፡ የምፈልገውን ነገር በግድ ማግኘት አለብኝ ትላለች፡፡ ሊያቷ ቀይ ጫማ አይሆንልሽም፤ ያስቸግርሻል ሁሉም ቦታ አድርገሽ መሔድ አትችይም ብትላት አልሰማ ስላለች ገዛችላት፡፡*

በተማሪ መፅሐፍ ላይ *ደራርቱ* የሊያትዋን ምክር እምቢ ብላ ቀዩን ጫማ ማድረግዋን የሚያሳይ ሲሆን፡፡ ቀዩ ጫማ እንደ ባህል አምልኮ ሰውን ያስሮጣል ተብሎ ስለሚታመን በሁለተኛው ስእል እንደተመለከተው *ደራርቱን* አስሩጦ ይዝዋት ሲጠፉና ዱር ሲከታት የሚያሳይ ነው፡፡

መምህር ቪድዮውን መግኘት ካልቻሉ ታሪኩን ለተማሪዎች ስእላዊ በሆነ የአተራረክ ዘዴ ይተርኩላቸውና ከታሪኩ ምን እንደተማሩ እየተነሱ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪ ከዚህ ቪድዮ ውጪ ለልጆች ይሆናል ብለው የሚያምኑበትን ካለ የትምህርቱ አካል ማድረግ

ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም ከዩትና ካዳመጡት የተረዱትን እንዲናገሩ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ምላሻቸውን ተቀበሏቸው፡፡ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

የመልመጃ አንድ መልስ

1. *ደራርቱ* የአያትዋን ምክር ያለመስማትዋ ለምን አይነት ችግር አጋለጣት የሚለውን ከጠየቁ በኋላ ግንዛቤያቸውን አንድ በአንድ አድምጡ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎቹ እንደሚከተለው ከመለሱ መልሳቸው ተክክል መሆኑን ያረጋግጡላቸው፡፡

*ደራርቱ* የአያትዋን ምክር ያለመስማትዋ

- ቀዩ ጫማ ከፍላጎትዋ ውጪ አስሩጦ ወስዶ ዱር ከተታት

የተለያዩ የትረካ ጨዋታዎችን ማያያዝ

ይህ ጨዋታ በጣም አስደሳች ስለሆነ ልጆች በተመለከቱት ምስል ላይ በመመርኮዝ ክብ ሰርተው አንድ ተማሪ ትረካውን እንዲጀምር በማድረግ ሌሎቹ ደግሞ ተቀብለው ታሪኩን እንዲያሟሉ ማድረግ ነው፡፡ *ደራርቱ* ወይም የቀዩ ጫማ ታሪክ በዚህ አይነት ሁኔታ አንድ ተማሪ ለሌላ እንዲነግር አድርጉ፡፡

ስለ ተመለከቱት ውይይትና ስላደመጡት ቀዩ ጫማ ትረካ አንዱ ለሌላው እንዲነግር አድርጉ፡፡

መምህር አስቀድመው ታሪኩን እርሶ ይጀምሩላቸው፡፡

ለምሰሌ፡ ካራን በልጅነቷ ከእናቷ ጋር ትኖር ነበር፡፡

አንድ ተማሪ ፡ እናትዋ በጣም ትታመም ነበር፡፡

ሌላ ተማሪ፡ ሀብትም አልነበራትም፡፡

ሌላ ተማሪ፡ ስለዚህ እናትዋ ለ*ደራርቱ* ከእንጨት ጫማ ትሰራላት ነበር፡፡ ወዘተ

መምህር ልጆቹ ሲናገሩ እርሶ በደንብ ይከታተሉ፡፡ ትረካው ቅደም ተከተሉ እንዳይዛባ እየተከታተሉ ማስተካከያ ይስጡ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በየተራ ትረካውን እንዲተርኩ

እድል ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም አድናቆትዎን ገልፀውላቸው ለራሰቸው እንዲያቸበጭቡ ያድርጉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ምልከታ
- ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በማድረግ
- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ

# ምእራፍ ሁለት   የፈጠራ ችሎታ

(የተሰጠው ክፍለ ግዜ 27 ክፍለ ጊዜ

የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የቤተሰብ አባላትን ድርሻ በመስመሰል መጫወት ያችላሉ፡፡
- የተለያ የመስመር አይነቶችን ያሰምራሉ፡፡
- መስመሮችን በማገናኘት የተለያዩ ቅርፆችን ይስላሉ፡፡
- የተለያዩ ነገሮችን በደብተራቸው ይነድፋሉ፡፡
- የነደፉትን ንድፍ ቀለም ይቀባሉ፡፡

የምእራፉ ዋና ዋና ነጥቦች

2.1 ተፈጥሮን ማድነቅ/6

2.2 ቤተሰብን ድርሻ ማስመሰል/ 8 ክፍለ ጊዜ

2.3 መስመሮችን ማሰማመርና ማቅለም /7 ክፍለ ጊዜ

2.4 የቤተሰብ መዝሙር በቀላል ምቶች መዝፈን/6 ክፍለ ጊዜ

## 2.1. የሰማይና የምድር ፍጥረት

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 6

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናፀፏቸው የሚገቡ ብቃቶች

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የሰማይና ምድር ፍጥረትን በመረዳት ይገልፃሉ፡፡
- በሰማይና በምድር ላይ ያሉ ነገሮችን በመዘርዘር ስለ አፈጣጠራቸው አድናቆታቸውን ይገልፃሉ፡፡

የዚህ ትምህርት ይዘት ዋና ሀሳብ

ተፈጥሮን ፡- ሰማይ ምድር ፀሐይ ጨረቃ አበባና የመሳሰሉትን በማየት መገንዘብና ማድነቅ፡፡

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

የተለያዩ የተፈጥሮ ገፅታዎችን የሚያሳዩ ስእሎች

የማስተማያ ዘዴ

መምህር ተማሪዎችዎ በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ ያሉትን ስእሎች እንዲመለከቱና በምስሎቹ ላይ ስለ ተመለከቷቸው ነገሮች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡ ተማሪዎቹም አንድ ባንድ እየተነሱ ምን ምን እንደተመለከቱ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎችዎን ከመማሪያ ክፍል ውጪ ይዘዋቸው በመውጣ የሰማይና የምድር ፍጥረትን እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ለይተው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ ለምሳሌ፡ የሰማይ ፍጥረታት ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ወዘተ የምድር ፍጥረታት አፈር ተክሎች ውሀ

ከምልከታ መልስ ከፍጥረታት የትኛው እንደሚያስደንቃቸው በየተራ እየተነሱ እንዲናጉ ያድርጓቸው፡፡በመቀጠል ባዩት ነገር ምን እንደተሰማቸው ተራ በተራ እንዲናገሩ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን ተቀበልዋቸው፡፡ በገለፃቸው ወቅት ሀሳባቸውን መግለፅ የሚያዳግታቸውን ተማሪዎች ይርዷቸው፡፡

## 2.2. የቤተሰብ የስራ ድርሻን ማስመሰል

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 8

መምህር የልጆች የአእምሮ ብስለት የሚመጣው በዙሪያቸው ስላሉ ነገሮች ክንውኖችን በማስመሰልና በመጠየቅ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ለልጆች የሚቀርቡት ቤተሰቦቻቸው ስለሆኑ ቤተሰቦቻቸው የሚያከናውኑትን ነገሮች ልጆቻቸው በቀላሉ ለማስመሰል ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ቤተሰቦቻቸው በቤት ውስጥ ምን ምን እንደሚሰሩ በመጠየቅ ይጀምሩ፤ከዚያም እያንዳንዱ ተማሪ የቤተሰቡን ስራ ከተናገረ በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ ያለውን ስእል እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡

በመቀጠል ተማሪዎቹ እናት ወይም አባት የሚሰሩትን በማስመሰል እንዲያሰዩ አድርጉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ልጆች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን መሳሪያዎች አቅርቡላቸው ፡፡ ልጆች መሳሪያዎችን ካገኙ ቤተሰቦቻቸውን የማስመሰል ስሜት በቀላሉ ሊመጣባቸው ይችላል፡፡

መምህር ይህን ትምህርት ለማስተማር የሚረዳዎትን መሳሪያዎች ወደ መማሪያ ክፍል ማምጣት ይኖርቦታል ለምሳሌ፡-

ሳህን

ብርጭቆልጆችን የሚወክል አሻንጉሊት

ጡጦ

ማንኪያ ጀበና እና ስኒ መፅሐፍ ስልክ መጥረቢያ

ማጭድ



የመሳሰሉትን በመጠቀም የቤተሰባቸውን የስራ ድርሻ እያስመሰሉ እንዲጫወቱ አድርጓቸው፡፡ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

በሌላ መልኩ በተማሪ መፅሐፍ ላይ እንደሚታየው የእናትና አባት አለባበስና ባህሪ ማስመሰል እንዳለባቸው አግዟቸው፡፡





መምህር  በመጨረሻም በመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለውን የመልመጃ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡



ልጆች የእናትና አባታቸውን የሚመስል ልብስ በመልበስ እንዲያስመስሉ ያድርጉ፡፡ልጆች የእናቶችን እንዲያስመስሉ ደግሞ የአባቶችን አለባበስ አካሄድና አነጋገር አስመስለው ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ አግዟቸው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

- ምልከታና የግልና የቡድን ገለፃ
- የግልና የቡድን አውደርእይ
- ፖርትፊሊዮ

## 2.3. መስመሮችን በማስመር ማቅለም

ለዚህ ርእስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ -9

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናፀፏቸው የሚገቡ ብቃቶች

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- መስመር በማስመር ያቀልማሉ
- የመስመር አይነቶችን በማስመር ይለማመዳሉ
- መስመሮችን በማቀናጀት ቅርፅ ይሰራሉ
- በመስለሮች ቅርፅ ሰርተው ቀለም ይቀባሉ

አበይት ነጥቦች

ምልከታ ማለት ማስተማር የተፈለገውን በመድረስ በአካል በመገኘት እንዲረዱ ማድረግ ነው ፡፡ በምልከታ ጊዜ በመማሪያ ክፍል በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢና በቤታቸው አካባቢ ስለማይገኙ ነገሮች በአካል ደርሰው በማየት ሚማሩት ነው፡፡ ይህም ልጆች ከአካባቢያቸው ጋር እንዲተዋወቁ ይረዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የቤተሰባቸው አባል እንዴት እንደሚጫወት እንዴትስ ወንዝ እንደሚሻገር የመሳሰሉትን እንዲለዩ አድርጓቸው፡፡

የመጀመሪያ ዝግጅት

ይህነ ርእስ ለማስተማር ለፅንሰ ሀሳቡ የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች እንደ እርሳስ፣ የቀለም እርሳስ፣ ቀለምና የውሀ ቀለም የመቀቢያ ቡሩሽ ወረቀትና የመሳሰሉትን ማዘጋጅት፡፡

መምህር የመጀመሪያ ዝግጅቶን ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች አስቀድመው እንዲያዘጋጁ በመንገር የቀኑን ትምህርት መጀመር

የማስተማሪያ ዘዴዎች

የሁለትዮሽ የቡድንና የክፍል ሙሉ ተማሪዎች ውይይት

የቡድን ስራ

ጥያቄና መልስ

## የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የሚለማመዱበት ክፍል
- የውሀ ቀለምና መቀቢያ ብሩሽ
- እርሳስ ቀለም እርሳስ ወረቀት የመሳሰሉት

## ተከታታይ ምዘና

- የግልና የቡድን ንፅብራቅ
- የክፍል ውስጥ ልምምድ
- ቤት ስራ
- ቃለ መጠይቅ

የልምምድ ጥያቄዎች መልስ

ልምምድ 1. ቋሚ መስመርን በመደጋገም መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ቋሚ መስመሮችን በማሰማመር እንዲለማመዱ ማድረግ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ቋሚ መስመር እንዲመለከቱ አድርጉ
- ቋሚ መስመሩን በሰሌዳ ላይ ከላይ ወደ ታች በማስመር አሳዩ
- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን መስመር ምሳሌ በመውሰድ በደብተሮቻቸው ላይ አኑሩላቸው
- በደብተራቸው ላይ የተሰጣቸውን ምሰሌ በማድረግ እነርሱ ሌሎች ቋሚ መእመሮችን እያሰመሩ እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 2 አግድም መስመርን በመደጋገም በማስመር መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች አግድም መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ ማድረግ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን አግድም መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- አግድም መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ
- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን  አግድም መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 3  ሰያፍ መስመር

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ሰያፍ መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ ማድረግ |

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ሰያፍ  መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- ሰያፍ መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ
- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን  ሰያፍ መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 4 ጠመዝማዛ መስመርን ደጋግሞ በማስመር መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ጠመዝማዛ መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ አድርጉ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ጠመዝማዛ መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- ጠመዝማዛ መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ

- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን ጠመዝማዛ መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 5 ዚግዛግ መስመርን በመደጋገም መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ዚግዛግ መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ አድርጉ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ዚግዛግ መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- ዚግዛግ መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ
- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን ዚግዛግ መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ ስድስት ሽክርክር መስመርን ደጋግሞ በማሰማመር መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ሽክርክር መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ አድርጉ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ሽክርክር መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- ሽክርክር መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ
- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው

- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን ሽክርክር መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 7 ክብ መስመርን ደጋግሞ በማስመር መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ክብ መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ አድርጉ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ክብ መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- ክብ መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ
- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን ክብ መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 8 ሞላላ መስመርን ደጋግሞ በማስመር መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ሞላላ መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ ማድረግ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን  ሞላላ መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- ሞላላ  መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ
- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን  ሞላላ  መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 9 የደጋን መስመር ደጋግሞ በማስማር መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ደጋን መስመርን በማሰማመር እንዲለማመዱ አድርጉ |

መምህር

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ደጋን መስመርን እንዲመለከቱ አድርጉ፡፡
- ደጋን መስመርን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ በማስመር አሳዩ
- በተማሪው መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመውሰድ በተማሪዎች ደብተር አኑርላቸው
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠትን ደጋን መስመር በማስመር እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 10 የተማሯቸውን የመስመር አይነቶች ደጋግሞ መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ከልምምድ 1-9 የተማሩትን መስመር አያነቶችን በመስራት እንዲለማመዱ ማድረግ |

መምህር

- አስቀድመው የመስመር ዓይነቶችን በሰሌዳ ላይ አሰምሩ
- እያንዳንዱን መስመር ካሰመርክ በኋላ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ምንን እንደሚመስሉ ተማሪዎችን ጠይቁ
  ለምሳሌ፡ ቋሚ መስመር የቆመ እንጨት መምሰሉን አግዳሚ መስመርን ደግሞ የቆመ እንጨትን አግድም ስናስተኛው የሚመስለውን

ሰያፍ መስመር በፍጥነት የሚንቀሳቀስን ሰው መምሰሉን ሞላላ መስመር ደግሞ ፊት ለፊት ሲታይ ምግብ መመገቢያ መምሰሉን

- የመስመር አይነቶችን ስሞች ንገራቸው
- እያንዳንዳቸውን የመስመር አይነቶች ከሰሌዳ ላይ በመጠየቅ አግዝ
- በመስመር የሚሰሩትን ቅርፆች ቀለም እንዲቀቡ አለማምድ የሚገኙትን ቅርፆች

- ከዚህ በመቀጠል የመስመር አይነቶች ምን አይነት ቅርፆች እንዳሏቸው በማሳየት መለየታቸውን አረጋግጡ

መልመጃ 1. የሚመሳሰሉትን ቅርፆች ማዛመድ

| |
|---|
| በዚህ መልመጃ ተማሪዎች የሚመሳሰሉትን ቅርጾችን እንዲለዩ ማድረግ |

መምህር

በመስመሮች ተሰርቶ በተማሪዎች ደብተር ላይ የተሰጠውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ እንዲያዛምዱ አለማምዱ

የመልመጃ አንድ መልስ

1. ረ 2. መ 3. ሠ 4. ለ 5. ሐ 6. ሀ

ልምምድ 11 በመስመር የተፈጠረውን ቅርፅ ከለዩ በኋላ ቀለም በመቀባት መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች የተጠየቁትን ቅርፅ ቀለም በመቀባት እንዲለማመዱ ማድረግ |

መምህር

- በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ የተቀመጡ የልምምድ 11 ቅርፆችን እንዲለዩ አድርግ
- በልምምድ 11 ስር ያሉትን ቅርጾች በሰሌዳ ላይ በመንደፍ አሳዩ
- በልምምድ 11 ስር ያሉትን ቅርጾች በተማሪዎች ደብተር ላይ በመንደፍ አግዙ
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተቀመጠውን ቅርጽ ቀለም በመቀባት እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 12 በመስመር የተሰራን ቅርፅ ቀለም በመቀባት መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች የተጠየቁትን ቅርፅ ቀለም በመቀባት እንዲለማመዱ ማድረግ |

- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የተቀመጡ የልምምድ 12 የተለያዩ ቅርጾች እንዲለዩ አድርጉ
- በልምምድ 12 ስር ያሉትን ቅርጾች በሰሌዳ ላይ በመንደፍ አሳዩ
- በልምምድ 12 ስር ያሉትን ቅርጾች በተማሪዎች ደብተር ላይ በመንደፍ አግዙ
- በተማሪዎች ደብተር ላይ የተቀመጠውን ቅርጽ ቀለም በመቀባት እንዲለማመዱ አድርጉ

ልምምድ 13 በመስመር የቤትን ቅርፅ በመስራት ቀለም በመቀባት መለማመድ

| |
|---|
| በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ኋላና ፊቱን በመጠበቅ የቤትን ቅርፅ ከነደፉ በኋላ ቀለም በመቀባት እንዲለማመዱ አድርግ |

መምህር

- በመጀመሪያ በአግዳሚና ቋሚ መስመር እስኴር ቅርጽ እንዲነድፉ አድርጉ
- በመቀጠልም ሶስት ጎነን በአግድምን በሰያፍ መስመር ከነደፉ በኋላ ከእስኴር ጋር በማገናኘት እንዲያስመስሉ አድርጉ
- በእስኴር መካከል በአግድምና ቋሚ መስመር አራት ጎን እንዲያስቀምጡ አድርጉ፡፡ ይህም በርን ለማሳየት በአራት ጎን ስር ሌላ አራት ጎን በመጨመር በሱ ትክክል አግድም መስመር እንዲያሰምሩ አድርጉ በመጨረሻም አራት ጎኑን በቀኝና በግራ እስኴሩን በማሳነስ እንዲያስቀምጡ አድርጉ፡፡ ይህም መስኮትን ለማሳየት እንደሚያግዛቸው ይንገሯቸው በዚህ አይነት ሁኔታ ከነደፉ በኋላ ቀለም እንዲቀቡ አስገንዝብ
- በመጫረሻም የሚሰሩትን ነገር በየግላቸው ተነስተው አንዱ ለሌላው በማሳየት ተራርመው ስለ ስራዎቻቸው እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡

## 2.4. የቤተ-ሰብ መዝሙር

ለዚህ ርእስ የተሰጠ የክ/ጊዜ ብዛት---7

ከዚህ በታች እንደተመለከተው ፊትና ኋላን በመጠበቅ የቤተሰብን መዝሙር ማስተማር

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናፀፏቸው የሚገባቸው የመማር ብቃት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- መዝሙር መዘመር መቻላቸውን ያሳያሉ
- ከሚዘምጋር በማያያዝ የቤተሰቦቻቸውን አባለት ይዘረዝራሉ ሩት መዝሙር

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ከበሮ

የመለማመጃ ክፍል

የባህል ልብስ

**የማስተማርያ ዘዴ**

መምህር ቀድሞ በማሳየት

ተማሪዎች መስመር በመስመር በመከፋፈል አስቀድሞ የመዝሙሩን ግጥም በመቀጠልም ዜማውን እራሳቸውን እስኪችሉ ማለማመድ

**ተከታይ ምዘና**

በዝግታና በፍጥነት የሚማሩ ተማሪዎችን በመለየት ሁለቱንም እንደየችሎታቸው ተጨማሪ ስራ በመስጠት እያገዙ ወደፊት ማስኬድ በዝግታ የሚማሩትን ደግሞ ተጨማሪ ሰአት በመስጠት ጉድለታቸውን እንዲያሟሉ በማገዝ በየቀኑ የሚያሳዩትን መሻሻል ለማወቅ ማስታወሻ እየያዙ መሄድ አስፈላጊ ነው ፡፡ / የተማሪዎች ፖርትፎልዮ ማዘጋጀት/

መምህር

ለመዝሙሩ በራስዎ ወይም ሌሎች ሰዎችን በመጋበዝ ዜማ ከሰሩለት በኋላ አስቀድመው እርስዎ በደንብ ተለማመዱ

ተማሪዎች መዝሙሩን ከመዘመራቸው በፊት ግጠሙን መስመር በመስመር አንብቡላቸው እነርሱም ከእርሶ እየተቀበሉ

እንዲለማመዱ አድርጉ

ግጥሙንበደንብ ከተለማመዱ እና ምንበብ ከቻሉ በኋላ ዜማውን ቀስ በቀስ አስቀድመው በመዘመር ያሰሟቸውና እነርሱም እርሶን ተከትለው ደግመው ተደማምጠው እንዲለማመዱ አድርጉ፡፡

በመጨረሻም በግልና በቡድን በመለማመድ ቆመው እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

**የልጆች መዝሙር**

**ለእናት መዘመር**

ትግስተኛዋ እናቴ
ሁሌ አስብሳለሁ መዳኒቴ
ወልደሽ ያሳደግሽኝ እናቴ
መጥቼ እሰካይሽ ናፍቂያለሁ
እናቴ ከልቤ ወድሻለሁ
ኑሪልኝ ለዘላለም
እንዳንቺ ሚሆን ለኔ የለም/×2

**ለአባት መዘመር**

የኔ ትግስተኛ አባት
እኮራብሀለሁ በእውነት
አሳድገሽኛል ጥሩ ሰው አድርገህ
በጣም ቸኩያለሁ መጥቼ እስከማይህ
ኑርልኝ ለዘላለም
እንዳንተ ሚሆን ለኔ የለም/×2

## የቤተሰብ መዝሙር



እናትና አባት

ወንድምና እህት

እነዚህ ባንድነት

የቤተሰብ አባለት/ x 2

ወንድም እህት አሉኝ

ሁሌ የሚያግዙኝ

ጥሩ ልጅ እንድሆን

ሁሌ የሚመክሩኝ /

ሌሎችም ዘመዶች

ከኛ ጋር ሚኖሩ

እየተጋገዙ ስራም የሚሰሩ

እነርሱም እንዲሁ ቤተሰቤ ናቸው

ስለ ፍቅራቸው ክብር ሚገባቸው

**የወንድም እና የእህት መዝሙር /የተማሪዎች መዝሙር**

**መምህር ከዚህ በታች ያለውን መዝሙር ከመዘመር በፊት የግንዛቤ ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት ምን ምን ዝግጅት መድረግ እንዳለባቸው የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማነቃቃት፤ በመቀጠለም ግጥሙን አስቀድመው በማንበብ እነርሱም እርሶን ተከትለው በግልና በቡድን ከተለማመዱና በሚገባ በግጠሙ ውስጥ ያሉትን ቃላት ካወቁ በኋላ ዜማው የሚታወቀውን ወንድሜ ያእቆብ መዝሙር አስቀድመው እርሶ በመዘመር ተማሪዎችዎ እርሶን እየተከተሉ እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡**

**2. 5. መዝሙርና ጭፈራ**





**ወንድሜ ያእቆብ** 2x

**ተኝተሀል ወይ** 2x

**ደውል ተደወለ** 2x

**ተነሳ** 2x

**ላ ላ ላ....**

**እሺ እነሳለሁ** 2x

**እጄን ታጥቤ**

ፊቴን ታጥቤ

ቁርሴን በልቼ

ወደ ትምህርት ቤት

እሄዳለሁ 2x



እህቴ ሜቲ 2x

ተኝተሻል ወይ 2x

ደውል ተደወለ 2x

ተነሺ 2x

ላ ላ ላ…

እሺ እነሳለሁ 2x

እጄን ታጥቤ

ፊቴን ታጥቤ

ቁርሴን በልቼ

ወደ ትምህርት ቤት

እሄዳለሁ 2x

**2.6. መዝሙርና ጭፈራ በቀላል ምት**

**ለዚህ ትምህርት ርእስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ 6**

**ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

**ከዚህ ርእስ ትምርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- መዝሙር መዘመር መቻላቸውን ያሳያሉ
- ከሚዘምሩት መዝሙር በማያያዝ ቀላል እንቅስቃሴ ያሳያሉ
- በግጥም ውስጥ ያሉትን ቃላት በማወቅ ያሰማሉ
- እጃቸውን አንድ ላይ በመምታት  በአንድ ምት አካሄድ በአንድነት በመዘመር ያሳያሉ

መግቢያ

ተማሪዎች ትምህርታቸውን በጨዋታ መልክ ይማራሉ፡፡ ይህንኑ በመደገፍ በዚህ ምእራፍ ውሰጠም የአካባቢያቸውን መዝሙር ከቀላል እንቅስቃሴ ጋር በማያያዝ የእጃቸውን ምት ፍጥነት አስማምተው በማስኬድ የባህላቸውን መዝሙር ማዳበር ይጀምራሉ፡፡

**አበይት ነጥቦች**

- መዝሙሮችን ከባህላዊ ጭፈራ ጋር
- የአካባቢ ባህል መዝሙር

የትምህርት  መርጃ መሳሪያዎች

- በአካባቢ ከሚገኙ ነገሮች  የሙዚቃ መሳሪያዎችን  ማዘጋጀት  ለምሰሌ ፡ ከበሮ ማሲንቆ ክራር
- በአካባቢ የሚገኙ ተጨማሪ መዝሙሮችን ማዘጋጀት

ተከታታይ ምዘና

በትምህርት አቀባበላቸው  ቀሰወተኛና ፈጣን የሆኑ ተማሪዎችን እንደችሎታቸው መጠን እያገዙ ማስኬድ ለምሳሌ ለቀስተኛ ተማሪዎች ተቸማሪ ሰአት በመመደብ ማስተማርና ለፈጣኖቹ ደግሞ ተጨማሪ ስራዎችን በመስጠት መገዝ ነው፡፡

መምህር ድርሻ

ለግንዛቤ የተቀመቱትን ጥያቄዎች እንዴት  እንዴት ያሉ ጭፈራዎችን እንደሚያውቁ በመጠየቅ የሚያውቁትን የጭፈራ አይነት እንዲናሩ በማድረግ የእለቱን ትምህርት መጀመር፡፡ በመቀጠልም ታዋቂ ልጆች ዘፈን ጨረቃ ድንቡል ዶቃ የሚለውን የልጆች መዝሙር በመጀመሪያ ግጥሙን ደጋግመው ያንብቡላቸው ተማሪዎቹ  እርሶን እየተከተሉ በግጥሙ ውስጥ ያሉትን ቃላት በደንብ እስይዙ ድረስ ይለማመዱ፡፡ በመጨረሻም በዜማ ይዘምሩላቸውና ተማሪዎችዎ ግጥሙን በዜማ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ራሳቸውን ችለው

መዘመር ከቻሉ በመስክ ላይ በቡድን በቡድን ሆነው እያጨበጨቡ እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡ በቡድን በሚጫወቱበት ወቅት የማይጫወት ልጅ እንዳይኖር በመቃኘት በማስተካከል ያከናውኑት፡፡

ጨረቃ ድንቡል ዶቃ

እዬ ቤት ገባች አውቃ

አዬ ቤት ያሉ ልጆች

ፈተጉ ፈታተጉዋት

በቁልፊት አስቀመጧት

ቁልፊቷ ስትሰበር

በዋንጫ ገለበጥዋት

አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ

ይችን ትተሽ ያችን ቆሎ

ያችን ቆሎ /2

ተግባር

ተማሪዎች ተመሳሳይ መዝሙሮችን ከሰዎች ጠይቀው ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ የቤት ስራ መስጠት፤ በአንድ ክፍለ ጊዜ እርሶ መጥነው እንዲያቀርቡ ያድርጉ ግን ሁሉም ተማሪዎች በሚቀጥሉት ክፍለ ግዚያቶች በየተራ እንዲያቀርቡ ቢደረግ መልክም ነው፡፡

# ምእራፍ ሶስት: የታሪክና የባህል ተጨባጭ ሁኔታ/

## 3.1 የህብረተሰቡና የአካባቢ ሙያዎች

ለዚህ ርእስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ --20

ቢያንስ ተማሪዎች ሎጎናፀጓቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ርእስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- አንዳንድ የቤት እቃዎች ከአፈር መሰራት እንደሚችሉ ያውቃሉ
- ልብስ ከጥጥ መሰራቱን ያውቃሉ
- ከእንጨት የሚሰሩ እቃዎችን ይዘረዝራሉ
- ከብረትና ከቆዳ ስራ የተለያዩ ጌጣጌጦች መሰራታቸውን ያደንቃሉ

አብይ ነጥቦች

የአካባቢ ስነጥበብና የህብረተሰብ ሙያ የሚባለው ከጥንት ጀምሮ በህብረተሰቡ ውስጥ ሲሰራበት የነበረ ነው፡፡ እነርሱም የሸክላ ስራ፣ ሽመና፣ የብረታ ብረት ስራ፣ የእንቾት ስራ፣ የቆዳ ስራና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የመጀመርያ ዝግጅት

ይህንን ርእስ ለማስተማር የአካባቢና የህብረተሰብ ስነ ጥበብ ሙያ  ከሞያው ጋር ሚያያዙ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማዘጋጀት፡፡

መምህር ዝግጅቶን ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎች የሚያስፈልገዋቸው ነገሮች አስቀድመው እንዲያዘጋጁ በመንገር የዝለቱን ትመህርት ጀምሩ፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ገለፃ
- የሁለትዮሽ ፣የቡድን እና ሙሉ ክፍል ምክክር

- በማሳየት የማስተማር ዘዴ
- ጥያቄና መልስ

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ከአፈር የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች
- ከተለያዩ ግብአቶች የተሰሩ ልብሶች
- የእንጨት ውጤቶች
- የብረት ስራ ውጤቶች
- የቆዳ ስራ ውጤቶች

## ተከታታይ ምዘና

- የግልና የቡድን ዕብረቃ
- የክፍል ውስጥ ልምምድ
- የቤት ስራ
- የቃል ጥያቄ

መምህር በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ስእሎች እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል እቃዎቹ ከምን እንደተሰሩ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡ በመጨረሻ በአካባቢቸው ከሚገኙ ነገሮች የሚሰሩ ባህላዊ እቃዎች ምን ምን እንደሆኑ እና አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

የመምህሩ ድርሻ

በተማሪ መፅሀፍ ከመልመጃ 1-6 የተሰጡትን መልመጃዎች አንድ በአንድ እየጠየቋቸው ምላሻቸውን ተቀበሏቸው፡፡ በትክክል የሚመልሱትን አድንቋቸው፡፡ ሌሎችም ደግሞ ለመመለስ እንዲንቀሳቀሱ ያበረታቷቸው፡፡

የመልመጃ አንድ መልሶች

ጀበና፣ ድስት፣ ምጣድ፣ ወዘተ ብለው ከመለሱ ጥሩ ነው፡፡

የመልመጃ ሁለት መልሶች

ጋቢ፣ ቡልኮ፣ እጀጠባብ ፣የአንገት ልበስ፣ ቀሚስ ፣ ወዘተ ብለው ከመለሱ ትክክል ነው ፡፡

የመልመጃ 3 መልሶች

መሶብ ፣ሰፌድ፣ እንቅብ፣ እርቦ ፣ወንፊት፣ ወዘተ ብለው ከመለሱ ትክክል ነው

የመልመጃ 4 መልሶች

ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ አልጋ፣ ዴስክ ፣ መስኮት፣ በር ወዘተ በማለት ከመለሱ በጣም ጥሩ ነው፡፡

የመልመጃ 5 መልሶች

ዶማ፣ አካፋ፣ ማጭድ፣ ድጅኖ፣ በር፣ መስኮት ወዘተ

የመልመጃ 6 መልሶች

ኮት ጃኬት ቀበቶ ጫማ ቦርሳ ወዘተ

## 3.2 የባህል መዝሙር

ለዚህ ርእስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ --8

| ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች |
|---|
| • ልጆች በባህል የሚጫወቱትን ጨዋታ መዝሙር ይዘምራሉ፡፡ |
| • አንዱ ለሌላው ተረት በመናገር ይጫወታሉ፡፡ |

መግቢያ

ተማሪዎች ባህላቸውን በተለያየ መንገድ እያዳበሩ መሔድ አለባቸው፡፡ ባህል ሠፊና በአንድ ጊዜ የሚማሩት ስላለሆነ በደረጃቸው የተለያዩ የባህል መዝሙሮችንና የቤተሰቦችቸውን የባህል ጨዋታ ጠይቀው አንዱ ለሌላው እነገሩና እየዘመሩ/እየዘፈኑ; እንዲማሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የትምህርት መርጃ መሳሪያ

ሙዚቃ መሳሪያዎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ ቁሳቁሶች ማዘጋጀት፣ ለምሳሌ ከበሮ ከበላ ክራር መስነቆና የመሳሰሉትነ ልጆቹ የሚመቻቸውን በአካባቢያቸው የሚታቁ መዝሙሮች በተጨማሪነት ማዘጋጀት፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ

መምህር አስቀድመው ከዚህ በታች የሚገኘውን የእንስሳት መዝሙር አስቀድመው በማንበብና ለመዝሙሩ ዜማ በበግሎት በመስራት ወይም ዜማ የመድረስ ችሎታ ያላቸው ሌሎች መምህራንን በመጋበዝ ወይም በዚህ ረገድ ሊያግዞት የሚችል ሌላ ሰው በመጋበዝ ካሰሩ በኋላ የህንን ትምህርት ማስተማሪያ ክፍለ ጊዜ ሲደርስ ተማሪዎችዎ የግጥሙን ቃላት መስመር በመስመር ያለማምዷቸው፡፡ ተማሪዎቹ የግጥሙን ቃላት በሚገባ መያዛቸውን ያረጋገረጡ፡፡ በመጨረሻ መዝሙሩን በዜማ እርስዎ ቀድመው እየዘመሩ ተማሪዎችዎ እርሶን እየተከተሉ በደንብ ይለማመዱ፡፡ ራሳቸውን ችለው መዘመር ሲችሉ በብድን በበድናቸው በመሆን አንዱ ሌላውን በማይረብሽበት ሁኔታ በማመቻቸት እንዲዘምሩ አድርጉ፡፡

የእንስሳት መዝሙር

በጎቹና ላሜ እንደምን ዋላችሁ

በዱር ስትውሉ ምን ምን ገጠማችሁ

በቂ ምግብና ውሀ አገኛችሁ

ወይስ ሳትበሉ ያማችሁን ዋላችሁ፡፡

በሬዎቹ የታሉ ፍየሎቼም ጭምር

እንዴት እንደዋሉ እረኛው ይናገር ፡፡

ግቡ በየተራ በየማደሪያችሁ

ተዘጋጅቶ ቀርቧል ይኸው አራታችሁ፡፡

ብሉ ጠጡ እረፉ  በየ መኝታችሁ

መልካም ለሊት ይሁን ሰላም ይብዛላችሁ/2

**ተከታታይ ግምገማ**

ቀስተኛና ፈጣን የትምህርት አቀባበል ያላቸውን ተማሪዎች  በመለየት ለፈጣን ተማሪዎች ተጨማሪ ስራ እንዲሰሩ በማድረግ ቀስተኛ የትምህርት አቀባበል ያላቸውን ተማሪዎች በማገዝ  የየእለቱን ለውጣቸውን በመመዝገብ ማከናውን ፡፡

**የልጅነት መዝሙር**

የልጅነት መዝሙር ታዋቂና በልጆች ዘንድ በጣም የሚወደድ ነው ፡፡ስለዚህ ተማሪዎቹ በቀላሉ እንዲረዱት ከዚህ በፊት መዝሙሮችን ለማስተማር እየተተቀሙ የመጡትን ዘዴ በመጠቀም ማለማመድና በደንብ ከተለማመዱ በኋላ በቡድን እና የክፍሉ ተማሪዎች በአንድ ላይ የሌሎች ክፍሎችን ትምህርት በማያስተጓጉል መልኩ እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

**የልጆች  ጨዋታ**

መምህር ከዚህ በታች የቀረበውን ጨዋታ ተማሪዎችዎን አጫውቱ ፡፡

ይህን ጨዋታ ለመጫወት ጠያቂና መላሽ ያስፈልጋል፡፡ ጠያቂው በፍጥነት በመደጋገም ይጠይቃል መላሾችም በፍጥነት ይመልሳሉ፡፡  በዚህ መካከል የተሳሳተ መልስ የሚሰጥ ልጅ ይሳቅበታል፡፡

ለምሳሌ፡የሚከተለውን ተጫወቱ ከዱር እንስሳት ውጪ የመለሰ ልጅ ይሳቅበታል ማለት ነው፡፡

1. ጠያቂ ፡ እንስሳት

   መላሽ: የዱር እንስሳት

   ጠያቂ: ምን ምን?

   መላሽ: ጅብ

ጠያቂ: ምን ምን

መላሽ፡ አንበሳ

ጠያቂ: ምን ምን

መላሽ፡ ነብር

2. ጠያቂ ፡ የሚበላ

መላሽ ፡ ምግብ

ጠያቂ ፡ ምን ምን?

መላሽ፡ እንጀራ

3. ጠያቂ ፡ የሚጠጣ

መላሽ ፡ ውሀ

ጠያቂ ፡ ምን ምን?

መላሽ ፡ ሻይ

**እነዚህ የመሳሰሉ ሌሎችንም በመጨመር ያጫውቸው፡፡ በመጨረሻም ልምምድ ሰባትን እንደሰሩ ያድርጉ፡፡**

# 3.3 ተረት ተረት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላተማሪዎች ፡-

- ተረት ወደ ቲያትር እንደሚቀየር ይገነዘባሉ
- ከአቅም በላይ መመኘት የሚያስከትለውን ጉዳት ይገነዘባሉ

**የመምህር ድርሻ**

በቅድሚያ ተረት ምን እንደሆነ ተማሪዎችዎን በመጠየቅ ጀምሩ፡፡

ተረት መተረክ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ ተራ በተራ በተማሪዎቹ ፊት ለፊት እየወጡ እንዲተርኩ አድርጉ

በመቀጠል ከዚህ በታች የቀረበውን የእርኩምንና ኤሊን ተረት ይተርኩላቸው፡፡

የንስርና ኤሊ ተረት

ንስርና ኤሊ አብረው ሲኖሩ አንድ ቀን ስለ ኑሯው ማውራት ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ንስር ኑሮ እንዴት ነው ስትል ኤሊን ጠየቃት፡፡ "ኤሊም ምን ትጠይቂኛለሽ አንቺ አለምን አዳርሰሽ ስትመጪ እንዳነቺ መሆን በጣም እመኛለሁ፡፡ አስቲ አንድ ቀን ይዘሽኝ ሂጂ አለቻት፡፡" ንስርም እኔ እንኳን ይዤሽ እሄድ ነበር አንቺ ግን በጠም ስለምትፈሪ ክንፌን ይዠሽ ስትንቀጠቀጪ ወድቀስ ትሰባበሪያለሽ አለቻት፡፡ በዚህ ጊዜ ኤሊ በፍፁም አልፈራም ውሰጅኝና ሂጂ አለቻት፡፡ በዚህ ጊዜ እርኩም በይ ተነሺ ክንፌን ያዥና አብረን እንሂድ አለቻት፡፡

ከዚህ በኋላ ንስር ሌሊን ይዛት ወደ ላይ ስትነሳ ኤሊ በጣም ፈርታ አይኗን ጨፈነች፡፡ ንስር እንዲህ አለቻት የአለምን ተአምር ማየት ከፈለግሽ አይንሽን ክፈቺ "ኤሊም እያለቀሰች በጣም ፈርቻለሁ በፍፁም አይኔን አልከፍትም" እባክሽ ወደ መሬት መልሺኝ ብላ ተማፀነች፡፡ በዚህ ጊዜ ንስር በአየር ላይ እንዳለች ወደ መሬት ለቀቀቻት፡፡ ኤሊም መሬት ላይ ተከስክሳ ሞተች፡፡

ይህ ተረት በርከታ እንስሳትን በማሳተፍ በቲያትር መልክ ቀርቧል፡፡

ምክንያቱም ተማሪዎችን ቀላል ታሪክ በመተረከረ የትያትር ገፀባህሪያት መቀያየር እንደሚችሉ ተገንዝበውና ተረድተው የትያትር ሙያ ከዚሁ እያሳደጉ እንዲሄዱ ታስቦ ነው ፡፡

መምህር ታሪኩን ተርከው ከጨረሱ በኋላ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያለውን ስእል በማሳይት ስለ ስእሉ ግምታቸውን እንዲናገሩ አድርጉ፡፡ ከዚያ በሀዋላ የተለያዩ እንስሳት በሳተፍ በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ እንደ ቲያትር የተጻፈው በዚሁ ተረት ተረት ላይ ተመስርቶ እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡

## 3.3.1 ተረት ተረት

ንሰርና ኤሊ



መምህር በተማሪው መፅኀፍ ለይ የለዉን ንሰርና ኤሊን

ተረት ደገግመዉ እንድጨዋቱ የድርጉ.

## 3.3.2 እንቆቅልሽ

ከባህላዊ ጨዋዎች አንዱ ሲሆን ጠያቂና መላሽ በጥንድ በጥንድ ሆነው ሊጫወቱት ይችላሉ፡፡ በጥንት ጊዜ ሰዎች ከስራ በኋላ የደከ አይሯቸውን ዘና ለማድረግና ጊዜ ለማሳለፍ ይጫወቱት የነበረ አሁንም ያለ ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡

መምህር ከዚህ በታች በስእል ተደግፎ የቀረበውን እንቆቅልሽ ተማሪዎችዎን በመጠየቅ አጫውቷቸው፡፡ተማሪዎችም የሚያውቋቸውን ሎሎች እንቆቅልሾች በመጠያየቅ እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡





1. አፍዋን ከፍታ ሰውን የምታይ= እንስራ



2. ጠዋት አይቻት ማታ አጣኋት= ጤዛ



3. መሬት ትሮጣለች ውሻ ትመስላለች= ቀበሮ



4. ህይወት ያለው ሙት የሚሸከም
ሙት ህይወት ያለውን የሚሸከም=
ፈረስና ኮርቻ



5. ሲበላ ይድናል ሲጠጣ ይሞታል= እሳት



**ተከታታይ ግምገማ**

- የቡድን ጨዋታ
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ

## 3.4 የአካባቢ ቀለማት

**ለዚህ ርእስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ**

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላተማሪዎች ፡-

- በአካባቢያቸው ያሉ ቀለማትን ይለያሉ
- በትምህርት ቤታቸው የሚገኙ ነገሮችን ቀለም ይለያሉ
- የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ባንዲራ ቀለምንና የአባገዳን አርማ ቀለም ይዘረዝራሉ
- በአካባቢያቸው ያሉ አበባትን ያደንቃሉ
- የአትክልትና ፍራፍሬ ቀለማትንና የእንስሳት ቀለማትን ይዘረዝራሉ

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

- ጉብኝት
- የጥንድ ውይይት
- በምልከታ
- ጥያቄና መልስ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

**ለዚህ ትምህርት ይዘት የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

- የመለማመጃ ክፍል
- የተለያዩ ስእሎች
- ፖስተር
- ሞዴል:

**ተከታታይ ምዘና**

- የቡድንና የግል ፅብረቃ
- የክፍል ውስጥ ልምምድ
- የቤት ስራ

- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ፈተና

የመምህር ድርሻ

- ተማሪዎች የአበቦችን ስእል ፣የአትክልትና ፍራፍሬ ፣የቤት እንስሰትን፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ባንዲራና የአባገዳን ስእሎች ከመማሪያ መፅሀፋቸው በመመልከት ቀለማቱን እንዲረዱ፣ እንዲለዩ፣ እንዲያ መሳስሉ፣ እንዲያደንቁ እንዲሁም በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንዲገነዘቡ በማድረግ ይህን የትምህርት ይዘት መጀመር ይቻላል፡ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ስእሎች ከጎበኙ በኋላ በጥንድና በቡድን እንዲወያ አድርጉ፡፡ የውይይታቸውን ውጤት ከቡድን በሚወከል ተማሪ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ካመቻቻችሁላቸው በኋላ በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንዲያደንቁ እና እንዲለዩ አድርጉ፡፡
- በየንኡስ ርእሱ የተሰጡ ተግባራት የተማሪዎችን የቀደመ ችሎታ እና እውቀት ለመቀስቀስ የሚረዳ ሰለሆነ ወደ ስእሎች ጉብኝት ከመግባታቸው በፊት በቡድን በቡድን ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ቢያድጉ ተማሪዎቹ በንቃት እንዲማሩ ያግዛል፡፡

- ከጉብኝት ስእሎች ውስጥ ጥቂቶቹን እንደ የቤትስራ እና የክፍል ስራ በመስጠት ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው በመምጣት ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ ይችላሉ፡፡

- የአካባቢያቸውን ቀለማት መለየታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ትክክለኛ ግብረ መልስ በመስጠት አካባቢያቸውን እንዲያደንቁና እንዲለዩ ማድረግ አለቦት፡፡

- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፏቸው ከሚገቡ የመማር ብቃቶች በላይ የሚሰሩ ተማሪዎች በሚያስተምሩበት ክፍል ያሉ ከሆነ መበረታታት አለባቸው፡፡ ተማሪዎቹ አውቂያለሁ ተገንዝቢያለው በማለት እንዳይዘናጉና በጥንካሪያቸው እንዲቀጥሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ቢያንስ ሊጎናጸፏቸው ከሚገቡ የመማር ብቃቶች በታች የሚሰሩ ተማሪዎች ካሉ ደግሞ ተጨማሪ እገዛ

ስለሚያስፈልጋቸው የተለየ ትኩረት ተሰጥቷቸው በትርፍ ሰአታቸው ተጨማሪ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

- አንዳንድ የተማሪዎችን ስራ በመምረጥ አስቀምጡ፡፡ ሌላ ጊዜ ወደ ክፍል በማምጣትና ክፍል ውስጥ በመደርደር እንዲያዩ በማድረግ እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡ በዚህ አይነት ስራዎቻቸውን እንዲጎበኙ ካደረጉ የተማሪዎችን የፈጠራ ስራ ፍላጎት የሚያነሳሳ ስለሆነ ተማሪዎች ስራዎቻቸውን እየወደዱ እንዲሄዱ ያደርጋል፡፡

ልምምድ 1 ፡ ቀለም መቀባት

በዚህ ስር ተማሪዎች በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ ያትን ስእሎች በደብተራቸው ወይም በወረቀት ላይ እንዲነድፉ ካደረጉ በኋላ ቀለም በመቀባት እንዲለማመዱ አድርጉ፡፡

**የመምህር ድርሻ**

- በተማሪ መፅሀፍ ያሉትን የአበባ ስእሎች እንዲለማመዱ አድርጉ ፡፡ በልምምድ አንድ ስር ያሉትን የአበባ ስእሎች እንዲነድፉና ቀድሞ የተቀባውን ቀለም በማየት አስመስለው እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡

ልምምድ 2: በአትክልትና ፍራፍሬ ላይ የሚታዩ ቀለማት

- በዚህ ትምህርት ስር ተማሪዎች በተማሪ መፅሀፍ ያሉትን ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ አድርጉ፡፡

**የመምህር ድርሻ**

- በልምምድ 2 ስር የሚገኘውን የአትክልትና ፍራፍሬ ስእል እየነደፉ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎቹ ንድፉን ከተለማመዱ በኋላ መጀመሪያ የተቀባውን ቀለም በማስመሰል ቀለም እንዲቀቡ አድርጉ፡፡

**የቤት እንስሳት ቀለማት**

መምህር በተማሪ መፅሀፍ ውስጥ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው የቤት እንስሳት ስእሎችን ተማሪዎቹ እንዲመለከቱ ካደረጉ በሀኋላ ቀለማቱን ለመናገር እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡

በመቀጠልም የቻሉትን ያህል በደብተራቸው እንዲነድፉና ቀለም መቀባት እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

እያንዳንዱ ተማሪ እየሰራ ያለውን ስራ በመመልከት ያበረታቷቸው፡፡ ደከም የሚሉትን ደግሞ ይርዷቸው፡፡ ስእሎቹን ለመንደፍ ካሁን በፊት የተማሯቸውን የመስመር አይነቶች መጠቀም እንደሚችሉም ይጠቁሟቸው፡፡

የአባ ገዳ አርማ እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባንዲራ ቀለማት፡፡

መምህር በተማሪ መፅሐፍ የቀረበውን የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ባንዲራና የአባ ገዳ አርማ ቀለማትን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም በልምምድ 6 ስር

ተማሪዎቹ የሚፈልጉትን አይነት ንድፍ በመንደፍ ቀለማትን በመቀባት እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

# ምእራፍ አራት : የስነ ጥበባት ማራኪነት

## 4. አስደናቂ የባህል ክንውኖች

ለምእራፉ የተመደበ ክፍል ጊዜ-25

### 4.1. የቤተሰብ መዝሙርና ውዝዋዜ

ለዚህ ርእስ የተመደበው ክፍል ግዜ--10

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- መዝሙር መዘመር መቻላቸውን በማድነቅ ያሳያሉ
- መዝሙሮችን በውዝዋዜ ያሳያሉ
- እያጨበጨቡ ይዘምራሉ፡፡

የቤተሰብ መዝሙርና ውዝዋዜ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ባህላዊ ወሳሪያዎች

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

- የመዝሙሩን ግጥም አስቀድሞ በመስመር በመስመር በማለማመድ
- በመቀጠል ግጥሙን በዜማ  እራሳቸውን ችለው እስከሚዘምሩ ማለማመድ

ተከታታይ ምዘና

በትምህርት አቀባበላቸው  ቀስተኛ የሆኑ እና ፈጣን የሆኑ ተማሪዎችን  በመለየት ሁሉንም እንደየ ችሎታቸው በማገዝ መካሄድ ፡፡ ለምሳሌ በቀስታ ለሚማሩ ተማሪዎች ተጨማሪ በመመደብ ፈጠን ላሉት ደግሞ ተጨማሪ የሚሰሩት ነገር በመስጠት

**የመምህር ድርሻ**

እስከ አሁን የተማሩትን መዝሙር  እንዲያስታውሱ በመጠየቅእና የትኛውን በይበልጥ እንደሚውዱ አንዱ ለአንዱ እንዲናገር በማድረግ

ከተማርዋቸው መዝሙሮች ሶስት ወይም አራት በመምረጥ እያጨበጨቡ ና ቀላል እንቅስቃሴ እያደረጉ ከ3-5 አባላት ባሉት ቡድን ተከፍለው እንዲለማመዱና ለክፍል እንዲያሳዩ በማድረግ

በመቀጠል ለሚቀጥለው ጊዜ እንደ የቤት ስራ ሰርተው በቡድን ተለማምደው እንዲያቀርቡ ከበቂ ጊዜ ጋር በሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ በመመርኮዝ በማሻሻል ይስጧቸው፡፡

1. እስከ አሁን ከተማራችኋቸው መዝሙሮች ስንት ታስታውሳላችሁ?
2. አስከ አሁን የተማራችኋቸውን መዝሙሮች ከውዝዋዜ ጋር ማሳየት ትችላላችሁ?

## 4.2. የቤተሰብን የስራ ድርሻ በድራማ መልክ መግለጽ፡፡

ለዚህ ርእስ የተመደበው ክፍል ጊዜ .... 10

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የቤተሰብን ድርሻ በመውሰድ መጫወትን ያዳብራሉ
- የቤተሰብ የስራ ድርሻን በመከፋፈል ስለ እሬቻ ያደንቃሉ
- የተውኔት ፅሁፍ አጥንተው የመጫወት ልምድ ያሳድጋሉ

**የይዘቱ ዋና ነጥቦች**

- በቲያትር መልክ የቀረበን የእሬቻ ባህል ክንውንን ማድነቅ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

- የመለማመጃ ክፍል
- የባህል ልብስ

- የተለያዩ ጌጣገጦች
- የምስል ድምፅ ማጫወቻ መሳሪያ የእሬቻ መዝሙር ዜማን ለማዳመጥ

**የመምህር ድርሻ**

- እሬቻ ምን እንደሆነ ተማሪዎች ማወቅ አለማወቃቸውን አጣራ
- የእሬቻ ባህል ክንውን ስእል ወይም ምስለ ድምፅ በማሳየት እንዲያስታውሱ አግዙ
- ልጆች በእሬቻ ላይ የሚኖረውን የቤተሰብ ድርሻ በመውሰድ በመጫወት እንዲያደንቁና እንዲረዱ ማድረግ
- የትምህርቱ ዋና አላማ ባህል ክንውኖች ማድነቅ በመሆኑ በተጨማሪ ልጆች ድርሻን በመውሰድ መጫውት/ሮል ፕላነገ እንዲያሳድጉ እሬቻ ላይ የቤተሰብን ድርሻ በመውሰድ እንዲጫውቱ አድረጉ
- እሬቻ ከኦሮሞ ህዝቦች ባህል አንዱና ቀዳሚ ነው፡፡ እሬቻ ማለት እግዚያብሔርን መለመን እና ማመስገን ነው፡፡ ልመናእና ምስጋናው የሚካሄደው በተወሰነ ቦታና ግዜ ነው፡፡

**የእሬቻ አይነቶች**

- እሬቻ በተለያዩ ቦታዎች ይካሄድ እንጂ ትልቁ/ዋናው በሁለት ቦታ ይከናወናል እነርሱም እሬቻ ቱሉ እና እሬቻ መልካ ናቸው፡፡

- እሬቻ አርፋሳ /እሬቻ ቱሉም ይባላል/ ይህ የሚከናወነው በተራራ ላይ ሲሆን ግዜውም በጋ አልፎ የበልግ ዝናብ በሚጠበቅበት ጊዜ ነው ፡፡ ያለፉት ወራት ዝናብ ጠፍቶ ድርቅ ሰዎችንና እንስሳትን ይጎዳ ነበር ስለዚህ በመጋቢት ወር አጋማሽ ሁሉም ሰው አርጥበትና ቅዝቃዜ ወዳለበት ቦታ በመውጣት የበልግ ዝናብ ለማግኘት እግዚያብሔርን /ፈጣሪን የሚለምኑበት ነው፡፡

- ወደ ተራራ ወጥቶ መለመን ድሮ ድሮ ከነበረው የኩሾች ዋቄፈና እምነት ጋር የተያያዘ ነው ይባላል፡፡ በኦሮሚያ ጩቃላ ተራራ ትልቁ የእሬቻ ቦታ ነው ፡፡

እሬቻ መልካ /እሬቻ ቢራ/

እሬቻ መልካ የሚከናወነው የክረምት ወቅት አልፎ በመስከረም ወር አጋማሽ /22--25/ ባሉት ቀናት ውስጥ ሲሆን የእሬቻ ቀን " አያና ብራ" ወይም ጠደቻ ሳቂ በመባልም ይታወቃል ፡፡ እሬቻ ብራ የሚከበርበት /የሚከናወንበት/ ቦታ መልካ እና ትላልቅ ሐይቆች ላይ ሲሆን በክረምት የወንዝ ሙላት ምክንያት ሳይገናኙ ተለያይተው የነበሩ እንዲገናኙ በማለት እንደ ጭለማ የሚታየው የክረምት ወራት አልቀው ለፍጥረታት ሁሉ ብርሀን የሚወጣበት በመሆኑ ይህንን ቀን እንደ ደስታ ቀን ይወስዱታል ፡፡ የጨለማው ክረምት አልፎ በባህርና ወንዞች ሙላት ዘመድና ቤተሰብ እንዳይገኛኝ የከለከለው የሚያልፍበት ጊዜ ስለሆነ



መምህር የእሬቻ ባህል ክንውንን የሚያሳዩትን ስእሎች በተማሪው መፅሀፍ ላይ ተመልክተው እንዲገምቱና እንዲናገሩ ያድርጉ ለምሰሌ የእናትና የአባት ዝግጅት እንዲሁም ጉረቤቶች እሬቻ ለመሄድ እራሳቸውና ልጆቻቸው ደረጉትን ዝግጅት በተመለከተ እንደሚከተለው እንዲጫወቱ አድርጉ፡፡

ህፃናት ጠዋት ከእንቅልፋቸው ተነስተው አይናቸውን እያሻሹ ወደ ውጪ ሲወጡ እናትና አባታቸው በባህል ልብስ አጊጠው ሳር በእጃቸው ይዘው ያያሉ፡፡
ወንዱ ልጅ -- እናቴ ዛሬ ሰርጋችሁ ነው እንዴ?
ሴትዋ ልጅ-- እኛን ከመውለዳቸው በፊት ነው ሰርግ ያደረጉት! ዛሬ ምን አለ? ምንድነው ቀኑ ዛሬ?

አባት--- ዛሬ እሬቻ ነው ልጄ!

እናት -- አዎ  የኔ ልጅ እናንተ ከእንቅልፋችሁ እስክትነቁ እየጠበቅናችሁ ነበር፡፡

ለናንተም ይኸው የባህል ልብስ ተዘጋጅቶላችኋል፡፡

አባት-- ጎረቤቶቻችንም በባህል ልብስ ተውበው እየጠበቁን ነው፡፡ ኑ እንሂድ

ወንዶችና ሴቶች ጎረቤቶቻቸው ይመጣሉ፡፡

*መምህር  በተማሪ መፅሀፍ ውስጥ የለዉን ስእላዊ መግለጫ አሳዩ.*





*መምህር ተማሪዎችዎን የእሬቻ መዝሙር እንዲዘምሩ ያለማምዷቸው*

| **አውራጅ** | **ተቀባይ** | |
|---|---|---|
| ገቢሰዮ ሆ ሆ | ገቢሰዮ ሆ ሆ | |
| ሮቤ ቢ.ያ ገቢ.ሴ | ሮቤ ቢ.ያ ገቢ.ሴ | |
| ኦሮሞን ኮርማ ቀሌ | ገቢሰዮ ሆ ሆ | ቢ.ያ ፈሌ ኮርሚሳ |
| ሮቤ ቢ.ያ ገቢ.ሴ | | |
| | ሮቤ ቢ.ያ ገቢ.ሴ! | |
| ኦዳ ሮባ ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| ኦዳ ቡልቱም ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| ኦዳ ነቤ ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| ኦዳ ብስል ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| ኦዳ ቡሉቅ ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| ሀዩ ቢ.ያ ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| ጃርሳ ቢ.ያ ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| መልካ ቱሉ ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |
| ዋቀ ኡማ ያ ቱመ ኮ! | ና ቱምስሜ | |

**ተከታታይ ምዘና**

- ጉብኝት
- የግልና የቡድን ፅብረቃ
- ፖርትፊልዮ
- የቃል ጥያቄ

## 4.3 የቤተሰብ ስእል

ለዚህ ርእስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ--6

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የእድሜ ባለፀጋዎች ከሚሰጡት ምክር ይማራሉ
- የተለያዩ ተግባራትን የሚያሰዩ የቤተሰብ ስእሎች ይለያሉ
- ቤተሰብ ልጆቻቸውን ምን ብለው እንደሚመክሩ ይዘረዝራሉ
- ልጆች በዚህ እድሜ ምን ምን እንደሚያከናውኑ ይገልፃሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

- ምልከታ
- ገለፃ
- የጥንድ የቡድንና የሙሉ ክፍል ውይይት
- ጥያቄና መልስ

**የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች**

ለዚህ የትምህርት ይዘት የሚያስፈልጉ የመርጃ መሳሪያዎች

- የመለማመጃ ክፍል
- የተለያ ስእሎች
- ፖስተር

- ሞዴል

**ተከታታይ ምዘና**

- የግልና የቡድን ፅብረቃ
- የክፍል ውስጥ ልምምድ
- የቤት ስራ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ፈተና

**የመምህር ድርሻ**

- አስቀድመው በተማሪ መፅሀፍ ላይ ያሉትን ስእሎች በማሳየት ስለ ምን እንደሆነ እንዲገምቱ ያድርጉ
  - በመቀጠል ቤተሰብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከነገሯቸው በኋላ እያንዳንዱን ስእል አጠገብ ላጠገብ በመያዝ መልእክቱን ንገሩዋቸው፡፡
  - በመጨረሻም ልጆች ከስእሉ ምን እንደተገነዘቡ በመከታተል ግብረ መልስ ይስጧቸው

# ምእራፍ አምስት: የስነ -ጥበባት ግንኙነት

ለዚህ ትምህርት የተመደበ ክፍለ ጊዜ --20

## 5.1. መዝሙር በቡድን በመዘመር የራስን ተፈጥሯዊ ድምፅ ማሳደግ

ለዚህ ትምህርት የተመደበ ክፍለ ጊዜ --12

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በቡድን የመዘመር ችሎታቸውን በመዘመር ያሳያሉ
- ከሚዘምሩት መዝሙር ጋር አያይዘው በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን በቡድን ይገልፃሉ
- ከሚዘምሩት መዝሙር ብዙ ቃላትን ይማራሉ

**የምእራፉ ዋና ነጥብ**

- *መዝሙሮችን በቡድን መዘመር*

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

በቀላሉ ከአካባቢ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

- **አስቀድሞ የመዝሙሩን ግጥም በመስመር በመስመር በማለማመድ ከዚያም ከዜማ ጋር እራሳቸውን ችለው መዘመር እስኪችሉ ድረስ በማለማመድ**

**ተከታታይ ምዘና**

**የግልና የቡድን ፅብረቃ**

**ልምምድ**

-በትምህርት አቀባበላቸው ቀስተኛ የሆኑ እና ፈጣን የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ሁሉንም እንደየ ችሎታቸው በማገዝ መካሄድ ፡፡ ለምሳሌ በቀስታ ለሚማሩ ተማሪዎች ተጨማሪ በመመደብ ፈጠን ላሉት ደግሞ ተጨማሪ የሚሰሩት ነገር በመስጠት

**የሀገር መዝሙር**

**የመምህር ድርሻ**

መምህር ካሁን በፊት ሰምተው የሚያውቁት የሀገር መዝሙር ካለ በመጠየቅ እርስ በእረሳቸው እንዲለማመዱ በቂ ግዜ በመስጠት በመጨረሻ ለክፍል እንዲያቀርቡ አበረታታቸው

.

**የቁጥርና የወራት መዝሙሮች**

**መምህር ድርሻ**

**ተማሪዎችዎ በተማሪ መፅሁፍ ያሉትን ቁጥሮች እንዲመለከቱ አድረጉ፡፡ በመቀጠል ከዚህ በታች ለግንዛቤ ያህል የቀረቡትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡**

1. የቁጥርና የወራት መዝሙሮች ሲዘመሩ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ቁጥሮችን መቁጠር ትችላላችሁ?

የተማሪዎችዎ መልስ አዎ እንችላለን ሊሆን ይችላል፡፡

መምህር በመቀጠል ተማሪዎች ከአንድ ጀምረው የቻሉትን ያህል እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡

1 ....2...3....4....5...

6...7....8....9.....10. .

11...12...13...14....15...

16. .17...18...19.....20.

30...40....50...60...70...80...90...100.

የአመቱን ወራት በቅደም ተከተል መናገር ትችላላችሁ በማለት ለተማሪዎችዎ ጥያቄ ያቅርቡላቸው፡፡ መልሳቸው አዎ ሊሆን ይችላል፡፡ ወራቱንም የቻሉትን ያህል እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

መስከረም ጥቅምት

ህዳር ታህሳስ ...... ብለን እንነሳለን

በተመማሪም የቁጥር ችሎታቸው እየጨመረ መሄድ ስላለበት ይህ እነዲሆን ቁጥሮችን በመዝሙር በቸዋታ ማስተማር በጣም ተመራች ነው ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን

የቁጥር መዝሙር እንዲዘምሩ አድርጉ፡፡ አስቀድመው የመዝሙሩን ግጥም መስመር በመስመር ራሳቸውን ችለው መናገር እስኪችሉ ድረስ ያለማምዷቸው፡፡ በመቀተል በዜማ ያለማምዷቸው፡፡ አስር አረንጓዴ መዝሙሮች የሚለው የቁጥር መዝሙር የሚታወቅ መዝሙር ስለሆነ እንደማያስቸግሮት እምነት አለኝ፡፡

**አረንጓዴ ጠርሙሶች መዝሙር**

አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ዘጠኝ ይቀራል፤
ዘጠኝ አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበርስምንትይቀራል፤
ስምንት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሰባት ይቀራል፤
ሰባት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ስድስትይቀራል፤
ስድስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አምስትይቀራል፤
አምስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አራት ይቀራል፤
አራት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሶስት ይቀራል፤
ሶስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሁለት ይቀራል፤
ሁለት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ
ድንገት አንዱወድቆ ቢሰበር አንድ ይቀራል፡፡×2

በተጨምሪም የሚያማምሩ ኳሶች መዝሙርን ልክ እንደ አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች ሁሉ በተመሳሳይ ዜማ ሁሌም እንደሚያደርጉት አስቀድመው የገጥሙን ቃላት ከጥሎ ከዜማ ጋር

በመጨረሻ ተማሪዎቹ በምስክ ላይ በቡድን በቡድን ሆነው እያጨበጨቡ እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡ ይህ ተማሪዎች በቀላሉ ቁጥር የመቁጠር ችሎታቸው እንዲጨምር ይረዳቸዋል፡፡

## የሚያማምሩ ኳሶች መዝሙር

የሚያማምሩ ዘጠን ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ስምንት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ስምንት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ሰባት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ሰባት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ስድስት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ስድስት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ አምስት ቀሩኝ
የሚያማምሩ አምስት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ አራት ቀሩኝ
የሚያማምሩ አራት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ሶስት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ሶስት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ሁለት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ሁለት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ አንድ ቀረኝ
አንደ ኳስ አለችኝ የታምር በጣም
በደንብ ይዛታለሁ እሷስ ከጄ አትወጣም ፡፡/×2

የቤት እንስሳት ና ንፅህናን የመጠበቅ መዝሙር  መዘመር

በተማሪ መፅሀፍ ላይ ያሉትን የእንስሳትና ንፅህናን የመጠበቅ መዝሙር ካሁን በፊት የተጠቀሙትን የመዝሙር ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጠቀም

ስተምሯቸው፡፡

## 5.2. የታሪካዊ ቦታዎች ግንኙነትና ትግበራ

**ለዚህ ርእስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ --8**

| |
|---|
| **ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች** |
| **ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-** |
| • የተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎችን ስእል በማየት ይለያሉ |
| • ታሪካዊ ቦታዎችን መገኛ ስእሎቹን በማየት ይገልፃሉ |
| • በተማሪ መፅሀፍ ላይ ያሉተን ታሪካዊ ቦታዎች በማየት ያደንቃሉ፡፡ |

.

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- ምልከታ
- ገለጻ
- የጥንድ የቡድንና የሙሉ ክፍል ተማሪዎች ውይይት
- ጥያቄና መልስ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

ለዚህ የትምህርት ይዘት የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- *የተለያዩ ስእሎች*
- *ፖስተር*
- *ሞዴል*

***ተከታታይ ምዘና***

- የግልና የቡድን ፅብረቃ
- የክፍል ውስጥ ልምምድ
- የቤት ስራ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ፈተና

## የመምህር ድርሻ

- አስቀድመው በተማሪ መማሪያ መፅሐፍ ላይ ያሉተን ስእሎች ተማሪዎች ተመልክተው ስለ ስእሉ ግምታቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ
- በመቀጠል ታሪካዊ ቦታዎች ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከነገሯቸው በኋላ በተማሪ መፅሀፍ ላይ ያለው እያንዳንዱ ስእል ምን እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡
- በመጨረሻም ልጆቹ ታሪካዊ ቦታዎችን መለየታቸውን በመከታተል ግብረ መልስ ይሰስጧቸው፡፡
- ከታሪካዊ ቦታዎች ስእሎች ምን እንደተገነዘቡ በመጠየቅ ግብረ መልስ ይስጧቸው ፡፡ በአካባቢያቸው የሚገኝ ታሪካዊ ቦታ ካለ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- በአካባቢያቸው ያለን ታሪካዊ ቦታ ከተናገሩ በኋላ በአካባቢያቸው ያለ ታሪካዊ ቦታ ህብረተሰቡ ታሪኩንና ባህሉን እንዲማርበትና ለመጪው ትውልድ የሚያወርሰው መኖሩን ጠይቋቸው ፡፡ ከዚያ በኋላ እነርሱም ታሪካቸውንና ባህላቸውን እንዲወዱና እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡

## የትምህርት ይዘቱ ዋና ዋና ነጥቦች

የኩምሳ ሞሮዳ ቤተ መንግስት የንጉስ ኩምሳ ሞሮዳ ቤተ መንግስት በ1881 በኦሮሞ ህዝቦችና በግሪኮች ትብብር ከተገነባ 130 ዓመታትን አስቆጥሯል ፡፡ የኩምሳ ሞሮዳ ቤተ መንግስት አስር ታሪካዊ የሆኑ ክፍሎች አሉት፡፡ ይህ ቤተ-መንግስት በነቀምት ከተማ ውሰጥ ይገኛል፡፡

መምህር ለልጆቹ ስለ ኩምሳ ሞሮዳ ቤተ- መንግስት ከነገሯቸው በኋላ በአካባቢያቸው ቤተ መንግስትና ታሪካዊ የሆነ ቦታ እንዳለ እንዲናገሩ ጠይቋቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ልጆቹ ታሪካቸውንና የህዝባቸውን ታሪክ እንዲወዱና እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡

## የአባጅፋር ቤተ መንግስት

የንጉስ አባጅፋር ቤተ መንግስት ከ140 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል ፡፡

የንጉስ አባጅፋር ቤተ መንግስት አምስት ዋና ዋና ቦታዎች አሉት ፡፡እነርሱም የንጉሱ መኖሪያ ቤት፣( ሱልጣን አባ ጆብር) የንጉሱ ልጆች መኖሪያ፣ የንጉስ አባጅፋር መኝታ ቤት፣ ትልቁ ቤተና መስኪድ ናቸው፡፡

መምህር ለልጆቹ ስለ ኩምሳ ሞሮዳ ቤተ- መንግስት ከነገሯቸው በኋላ በአካባቢያቸው ቤተ መንግስትና ታሪካዊ የሆነ ቦታ እንዳለ እንዲናገሩ ጠይቋቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ልጆቹ ታሪካቸውንና የህዝባቸውን ታሪክ እንዲወዱና እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡

ድሬ ሼክ ሁሴን

ድሬ ሼክ ሁሴን በባሌ ዞን ጎሎልቻ ወረዳ የሚገን ሲሆን ከኦሮሚያ ዋና ከተማ ፊንፊኔ 624 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የሚገኝ ነው፡፡

ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ 184 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከወረዳ ከተማው ጃራ ደግሞ 64 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገን ነው ፡፡

ድሬ ሼክ ሁሴን ከብዙ ዘመናት በፊት የሙስሊም እምነት ትምህርት የሚማሩበት ቦታ ሆኖ የቆየና እየተስፋፋ የመጣ ሲሆን በዚህ ወቅት ደግሞ የየትኛውም እምነት ተከታዮች ይን ታሪካዊ ቦታ በመጎብኘት የተፈጥሮን መስህብ ያደንቃሉ፡፡

ሐረር

ሐረር በአለም ከሚገኙ ከተሞችዉስጥ የቱሪዝም መስህብ ካላቸው ከተሞች አንዷ ነች፡፡ የከተማዋ ታሪክ ከ 1000 አመታት በላይ አስቆጥሯል ፡፡ የጀጎል ግንብና በሮቹ የወርቅ ሳንቲሞች ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ መስኪዶች የተለያዩ ግንባታዎችና የእጅ ጥበብ ስራዎች እንደሚገኙ ታሪክ ይመሰክራል፡፡

መምህር ለልጆቹ ስለ ሐረር ከተማ ከነገሯቸው በኋላ በአካባቢያቸው ታሪካዊ የሆነ ቦታ እንዳለ እንዲናገሩ ጠይቋቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ልጆቹ ታሪካቸውንና የህዝባቸውን ታሪክ እንዲወዱና እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡

## የጨለንቆ ሀውልት

የጨለንቆ ሀውልት በ ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ከጨለንቆ ከተማ 3 ኪሎሜትር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ቦታ በምኒሊክ ወረረ ግዜ በጅግናው በከር ዋሬ የሚመራው ብዙ የኦሮሞ ጦር የተሰዋበት ቦታ ነው፡፡ ይህ ጦርነት በ1887 እንደተካሄደ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ይህ የእልቂት ስፍራ እሰከ አሁን ድረስ ጨሊ ጨለንቆ በመባል ይታወቃል ፡፡ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተከፈተውን ጦርነት ተዋግቶ ሲያዋጋ የነበረው በከር ዋሬ ገዳ ይባላል ፡፡ በከር ዋሬ የራባ ዱሪ ጠር መሪ ነበር፡፡

ይህ ሀውልት በዚያ ዘመን ለኦሮሞ ህዝብ ሲሉ ለተሰው ሰዎች መታሰቢያ እንዲሆን ተሰራ፡፡ የአሁኑ ትውልድም ካለፈ ታሪክ በመማር እንደነዚህ ያሉ ታሪካዊ ቦታዎችን መንከባከብ ይጠበቅበታል፡፡

መምህር ለልጆቹ ስለ የጨለንቆ ሀውልት ተርከዊ ሁኔታ ከነገሯቸው በኋላ በአካባቢያቸው ታሪካዊ የሆነ ቦታ እንዳለ እንዲናገሩ ጠይቋቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ልጆቹ ታሪካቸውንና የህዝባቸውን ታሪክ እንዲወዱና እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡

## የአኖሌ ሀውልት

የአኖሌ ሀውልት በአርሲ ዞን ከኢተያ ከተማ 10 ኪሎ ሜትር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ቦታ በምንኒሊክ ወረራ ግዜ የኦሮሞን ህዝብ ወንዶችና ሴቶችን በአንድነት የወንዶችን ቀኝ እጅ የሴቶቹን ቀኝ ጡት የቆረጠበት ቦታ ነው፡፡

የአኖሌ ሀውልት የተሰራው በዚያን አመት መስዋእት ለሆኑ ሰዎች መታሰቢያ ነው፡፡ በኦሮሞ ታሪክ ውስጥ ያለፉትን ማጥናትና ማስታወስ የዛሬዎቹን ማጠናከር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ይህ ሀውልት ተገነባ ፡፡ በአኖሌ የተሰውት ሰዎች ማስታወሻም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

ዋና አላማው እንደዚህ ያሉ አስከፊ ተግባራት እንዳይደገሙና መጪው ትውልድ ከዚህ እንዲማርና እንዲያስተምር ይረዳል፡፡

መምህር ለልጆቹ ስለ የአኖሌ ሀውልት  ተርካዊ ሁኔታ ከነገሯቸው በኋላ  በአካባቢያቸው ታሪካዊ የሆነ ቦታ እንዳለ እንዲናገሩ ጠይቋቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ልጆቹ ታሪካቸውንና የህዝባቸውን ታሪክ እንዲወዱና እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡

**የአባ ሙዳ አዳራሽ**

የአባ ሙዳ ቱለማ  አዳራሽ  በቢሾፍቱ ከተማ  ሆዶ ቀበሌ በሚባል ቦታ ይገኛል፡፡  በገዳ ስርአት ውስጥ አባ ሙዳ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡  አባገዳ ወደ ስልጣን በሚመጡበት ጊዜ ስርአቱ በአባሙዳ ይከናወናል፡፡ የአባ ገዳ ድርሻ  በአባ ሙዳው የነገራል፡፡

ይህ የአባሙዳ አዳራሽ 2013 በገዳ ስርአት ውስጥ እንዳለው ትረጉም ተገንብቶ ስራ ላይ ዋለ ፡፡ የአሁኑ ትውልድም ስርአቱንና ታሪካዊ ቦታውን ተንከባክቦ ለትውልድ ማውረስ አለበት፡፡

መምህር ልጆች የአባ ሙዳ ቱለማን አዳራሽ ጥቅም ከነገሯቸው በኋላ በአካበቢያቸው የአባሙዳ አዳራሽ መኖሩን ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል እነርሱ ታሪካቸውንና ባህላቸውን እንዲወዱና.እንዲያደንቁ አድርጉ

**የመምህር ድርሻ**

1. ከዚህ በታች ያለውን  ታሪካዊ ቦታ የሚለውን ግጥም ለተማሪዎች በማንበብ እንዲያውቁት አድርጉ፡፡
2. የሚከተሉትን  የልጆች መዝሙር  እንደየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ በማያያዝ ያለማምዷቸው ፡፡ ከዚያም ልጆቹ ራሳቸውን ችለው እንዲዘምሩ አድርጉ

**የታሪካዊ ቦታ መዝሙር**

እኛስ  ብዙ አለን
ታሪካዊ  ቦታ
አንድ ሁለት ብለን
እንቁጠር በተርታ

የኩምሳ ሞረዳ
ደግሞም ያባ ጅፋር
የጨለንቆ ሀውልት
ጀጎል ግምብ ከሀረር

ቢሾፍቱ ላይ ያለው
ገልማ አባ ሙዳ
ሁልጊዜ ይነሳል
ሲሾም አባ ገዳ

የድሬ ሼክ ሁሴን
ባሌ ምድር ያለው
የቱሪስት መስህብ
ሁሉ ሚጎበኘው፡፡

አኩሪ ታሪክ አለን
እኛ አውቀን ለሌላ
እናሳውቃለን ×2

በአጠቃላይ በየክፍለጊዜው ትምህርት ከዚህ የሚቀጥሉትን ዋና ነጥቦች በመጠቀም አስተምሩ፡፡

የመማር ማስተማር

- ተከታትሎ በማሳየት
- ሰፊ ጊዜ በመስጠት የተሰቱ ተግባራትን እንዲለማመዱ በማድረግ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ከበሮ

- ከተቻለ ኪቦርድ ትንንሽ /ፒያኖ ጊታር
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ክራር ማሲንቆ

ተከታታይ ምዘና

- ተከታታይ ምዘን ሂደትን በመከተል የተማሪዎችን የየለት መሻሻል በማይት ግብረ መልስ በመስጠትና የተሸለ ውጤት ያስመዘገቡትን እየያዙ በመሄድ

**ታሪካዊ ቦታዎችን በቡድን ድርሳ በመውሰድ መጫወት**

ለዚህ ርእስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ---9

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በቡድን ውክልና በመውሰድ የመጫወትን ልምድ ያሳድጋሉ
- ታሪካዎ ቢታዎችን በትያትር ውስጥ ይረዳሉ

**የይዘቱ የትኩረት ነጥብ**

- የትያትር ሙያ ሌሎች ተምህርቶችን ለመማር ያለው ድርሻ
- ታሪካዊ ቦታዎችን በመወከል መጫወት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

- የመለማመጃ ክፈል
- ፊሽካ
- ጠመኔ
- ዳስር
- ፎቶ

**መምህር ድርሻ**

በዚህ ትምህርት ይዘት ስር በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ ተማሪዎች የተማሪና የመምህር ድርሻን በመውሰድ የሚጫወቱትን እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎችዎ ጋር

**ማን እንደ መምህር ሆኖ መጫወት እንደሚወድ በመጠየቅ ከለዩ በኋላ በፍላጎታቸው ላይ በመመርኮዝ የመምህር ድርሻና የተማሪ ድ እንዲጫወቱ አድርጉ፡፡**

**ስለዚህም ዘወትር እንደሚያደርጉት ሰፊ ግዜ በመስጠት አለማምዷቸው፡፡ በመጨረሻም እንዲያሳዩ አድርጉ፡**

**ለምሳሌ፡ የመምህርን ድርሻ የሚወስደው ተማሪ አለባበሱ /አለባበስዋ  ከተቻለ መነፅር አድርጎ/አድርፋ ጠመኔ ዳስተርና ፊሽካ እንዲይዝ /እንድትይዘ በማድረግ ፊሽካ በመንፋት ተማሪዎች ወደ ክፍል እንዲገቡ እንዲጠጣ/እንድትጠራ ያድርጉ፡፡**





**መምህር ፡ ሌንጮ ደብተርህን ለምን አታወጣም ?**



**ሌንጮ፡ ቤት ነው**

**ሁሉም ተማሪዎች ይስቃሉ**

መምህር ፡ ተናንት ስለ ኦሮሚያ ታሪካዊ ቦታዎች ተምረን ነበር ፡፡ እስኪ ዛሬ ተመልሰን እናስታውሰው? እኔ እጀምርላችኋለሁ እናንተ ደግሞ በቡድናችሁ መልሱ.



መምህር ኦሮሚያን እንዞራለን 2x

**ቡድን አንድ፡ ታሪካዊ ቦታ እንጎበኛለን**

መምህር፡ ከወለጋ እንጀምራለን

**ቡድን ሁለት፡ የኩምሳ ሞሮዳን ቤተ መንግስት እንጎበኛለን**



መምህር፡ በዛው ወደ ጅማ እንወርዳለን

ቡድን አንድ፡ የአባጅፋርን ቤተ መንግስት እንጎበኛለን



መምህር፡ አርሲ ጭላሎ ተራራ ላይ እንወጣለን

ቡድን ሁለት፡ የአኖሌን ሀውልት እንጎበኛለን



መምህር፡ ባሉ ባልዮ እንሂዳለን

**ቡድን አንድ ፡ ድሬ ሹክ ሁሴንን እንጎበኛለን**



መምህር፡ ሐረርጌ የፍቅር ሀገር እንሂዳለን

**ሁሉም ተማሪዎች  የጨለንቆን ሀውልት እንጎበኛለን**



**ሁሉም ተማሪዎች የጀጎልን ግንብ እንዞራለን**




## ተከታታይ ምዘና

- ★ በቡድን ማሳየት
- ★ የግልና የቡድን ገለፃ
- ★ ፖርትፎሊዮ
- ★ የቃል ጥያቄ

# የሥነጥበባት ትምህርት ሲለበስ

# አንደኛ ክፍል

**የመማር ዉጤቶች፡**

**በዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች:**

- በአከባቢያቸዉ የሚገኙትን ምስሎች፣ ቀለሞችና ድምፆች ይለያሉ፤
- ቀለል ያሉ ዝማሬዎችን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን ያስመስላሉ፤
- በአከባቢያቸዉ የሚገኙትን ሥነጥበባትይረዳሉ፣
- የሥነጥበብ ስራዎችን ያደንቃሉ፡፡

| የትምህርት ዐበይት ነጥቦች | ይዘት | የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች | ምዘናና ክትትል |
|---|---|---|---|---|
| ስነጥበባትን መረዳት | **ምዕራፍ** 1፡<br>1. ምልከታ (25 ክፍለ ጊዜ)<br>1.1 የምስሎችንና ክዋኔዎችን መልዕክት መለየት (8 ክፍለ ጊዜ)<br>1.2 ከክዋኔ ጋር ተዘጋጅተው የቀረቡ ቀለል ያሉ ዝማሬዎችን ማየትና ማዳመጥ (9 ክፍለ ጊዜ)<br>1.3 ቪዲዮ ወይም ምስል-ድምፅ ማየትና ማዳማጥ (8 ክፍለ ጊዜ) | ☞ ተማሪዎች ዝማሬዎችን፣ ቪዲዮዎችንና ምስሎችን እንዲሰሙና እንዲያዩ ማድረግ<br>☞ ተማሪዎች የምስል-ድምፆችን መልዕክት፣ ምስሎችና ክዋኔዎችን እንዲሰሙና እንዲያዩ ማድረግ | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ ምስሎችና የቪዲዮ ማጫወቻ<br>▪ የውዝዋዜ አልባሳት<br>▪ የተዘጋጁ ምስል-ድምፆች | • ምልከታ<br>• የግልና የቡድን ገለፃ/ፅብረቃ |
| የፈጠራ ክሂሎት | **ምዕራፍ** 2 ፡የፈጠራ ችሎታ<br>ስሜትን መግለፅ (Expression) (27)<br>2.1. የቤተሰብ ሚናን ማስመሰል<br>6 ክፍለ ጊዜ))<br>2.3. ቀላል መስመሮችን በማስመር ማቅለም (ክፍለ ጊዜ 8)<br>2.4. የቤተሰብ ዝማሬ (ክፍለ ጊዜ7)<br>2.5. በቀላል ምቶች ዉዝዋዜ ማድረግ (ክፍለ | ☞ የቤተሰብ መዝሙር ማዜም<br>☞ የቤተሰብ ሚናን በዜማ ማስመሰልና ድርሻ ተጫዉቶ ማሳየት<br>☞ ቀላል መስመሮችን በማስመር ማቅለም | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ እረሳስ፣ ክራወንና በአከባቢያችን የሚገኙ የንድፍ ስራ መሳሪያዎች | • ምልከታ<br>• የግልና የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ጊዜ 6) | | | |
| ባህላዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች | **ምዕራፍ** 3፡<br>3. **ባህል (20 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.1. በአከባቢና በማህበረሰብ ዉስጥ የሚገኙ የስነጥበብ ስራዎች (መዝሙር፣ ቀለማት፣ ዉዝዋዜ፣ ተረት ተረት፣ እንቆቅልሽና የልጆች ጨዋታ) (ክፍለ ጊዜ 7)<br>3.2. በአከባቢ ያሉ ቀለማት (ክፍለ ጊዜ 6) | ☞ በአከባቢና በማህበረሰብ ዉስጥ የሚገኙ የስነጥበብ ስራዎችን በማዜም፣ ሚና በመጫወትና በዉዝዋዜ በመከወን ማሳየት.<br>☞ የቤተሰቦቻቸዉንና የጓደኞቻቸዉን አልባሳት ቀለም ይለያሉ (የክልልና የሀገር ሰንደቅ አላማ) | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ እረሳስ፣ ክራወንና በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የንድፍ ስራ መሳሪያዎች | ▪ ምልከታ<br>▪ የግልና የቡድን ገለፃ<br>▪ ፖርትፎሊዮ<br>▪ የቃል ጥያቄ |
| የስነጥበባት ሳቢነት | **ምዕራፍ** 4፡<br>4. ባህላዊ ኩነቶችን ማድነቅ (ክፍለ ጊዜ 25)<br>4.1 የብተሰብ መዝሙሮችና ውዝዋዜ (ክፍለ ጊዜ 9)<br>4.1. የቤተሰብ ሚናን በድራማ መልክ መጫወት (ክፍለ ጊዜ 10)<br>4.2. የቤተሰብ ምስል (ክፍለ ጊዜ 6) | ☞ ተማሪዎች ዜማን፣ ዉዝዋዜን፣ ሚና መጫወትን፣ ነፃ የንድፍ ስራዎችን እየሰሩ በተግባር እንዲያሳዩ ማስተማር | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ እረሳስ፣ ክራወንና በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የንድፍ ስራ መሳሪያዎች | ▪ ምልከታ<br>▪ የግልና የቡድን ገለፃ<br>▪ ፖርትፎሊዮ<br>▪ የቃል ጥያቄ |
| ትስስር፣ ግንኙነትና | **ምዕራፍ** 5፡ | ☞ ተማሪዎች የተፈጥሮ ቀለማትን ሚና | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና | ▪ ምልከታ<br>▪ የግልና የቡድን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ተግባራዊነት** | 5. **አፈፃፀም/ተግባር** (20)<br>5.1. **በቡድን ሚና መጨወት** **የቡድን መዝሙር** (ክፍለ ጊዜ 12)<br>5.2. **የታሪካዊ ቦታዎች ትስስር፣ ግንኙነትና ተግባራዊነት፤ በዜማ ሚናን መጫወትና በምስል ማሳየት** (ክፍለ ጊዘ 8) | **በመጫወት በቀላል ምት እየተወዛወዙ እንዲያዜሙ ማነሳሳት** | **ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች** | **ገለፃ**<br>▪ **ፖርትፎሊዮ** |